
**Christian Gospel Conference**

# ክርስቶሰን መለማመድ፣ መደሰት እና መግለጥ

**“ኦክቶበር” 17-19, 2025**
**ሂውስተን፤ ቴክሳስ**

ክርስቶስን እንደ መለወጣችን ምሥጢር፣ ማለትም፣
በማንኛውም ዓይነት ከባቢ ሁኔታ፣ የግል ሁኔታ ወይም አጋጣሚ
ከተፈጥሯዊ ሕይወታችን በገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ እንደ መለወጣችን ምሥጢር
ልንማረው ያስፈልገናል፤ ይህ ተግባራዊ እና ቀላል ምሥጢር
ያለማቋረጥ ከጌታ ጋር መነጋገርን በተግባር መለማመድ ነው፤
ያኔ በቅጽበት ክርስቶስን እንኖራለን።

© 2025 Living Stream Ministry. መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከሪካቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለው አገልግሎት ከሊቪንግ ስትሪም ሚኒስትሪ በተገኘ በጎ ፈቃድ እንደገና የታተሙ ናቸው። በማንኛውም መልኩ አታባዙ።


Right turn only
Windswept Ln
Gate
Parking
Lot
Book
Room
Conference
Room
Registration
Baptism
Book
Sales
Children's Meeting
AV
Room
Registration
Closet
Games
Up
Snack
Singing
Craft
Activity
Room
Upstairs
Dining
Hall
Kitchen
Parking
Lot
Middle
Hall
Playground
Parking
Lot
Parking
Lot

## የኮንፍረንስ መርሐ-ግብር

**አርብ - ኦክቶበር 17**

7፡30 pm – 9:30 pm – 1ኛ ክፍለ ጊዜ
7፡30 – መዘመር እና መልእክት 1
8፡30 – ትንንሽ ቡድኖች
9፡00 – ሰላምታ እና ቀለል ያሉ ምግቦች እና እንግዶችን መቀበል
የስብሰባው መጨረሻ

**ቅዳሜ - ኦክቶበር 18**

10፡00 am – 12፡00 pm –2ኛ  ክፍለ ጊዜ
10፡00 – መዘመር እና መልእክት 2
11፡00 – ትንንሽ ቡድኖች
11፡45 – የምሳ ዕረፍት

12፡00 pm – 5፡00 pm – ዕረፍት እና የወንጌል ተግባራት
12፡00 pm – ምሳ
1፡30 – ለወንጌል መውጣት / ጉብኝቶች
4፡00 – የወንጌል ሪፖርቶች
5:30 pm – እራት

6፡45 pm – 9፡00 pm – 3ኛ ክፍለ ጊዜ 3
6፡45 – መዘመር
7፡00 – መልእክት 3
8፡00 –የአገልግሎቱን ጽሑፎች በቡድን ቡድን ሆኖ ማንበብ
8፡30 – በየቡድኑ የተሞላነውን ማካፈል
የስብሰባው መጨረሻ

**የጌታ ቀን - ኦክቶበር 19**

9፡30 – የጌታ ማዕድ
10፡00 – መዘመር እና መልእክት 4
11፡30 – የተሞላነውን ማካፈል
11፡45 – የመደምደሚያ ቃል
የስብሰባው መጨረሻ

## መልእክት አንድ

## በቅድስና ነቀፋ የሌለን የመሆናችን ምክንያቱ እና በመንፈሳችን፣ በነፍሳችን እና በሥጋችን ሙሉ በሙሉ የመቀደሳችን ምክንያቱ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ተሰ. 3፥13፤ 5፥23-24

**I. ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት የተቀደሰን ሕይወት እንኖር ዘንድ፣ ጌታ ልባችንን በቅድስና ነቀፋ የሌለበት (በቅድስናችን ምንም እንከን የማይገኝበት) አድርጎ ያጸናው ዘንድ ያስፈልገናል—1 ተሰ. 3፥13፡-**

ሀ. ልብ የሰው የውስጥ ክፍሎች ድምር፣ የሰው ዋናው ወኪል፣ የድርጊቱ ወኪል ነው፡-

1. ልባችን የነፍሳችን ክፍሎች ሁሉ—አእምሮ፣ ስሜት እና ፈቃድ (ማቴ. 9፥4፤ ዕብ. 4፥12፤ ዮሐ. 14፥1፤ 16፥22፤ ሐዋ. 11፥23) ሲደመር የመንፈሳችን አንድ ክፍል—ሕሊናችን (ዕብ. 10፥22፤ 1 ዮሐ. 3፥20) ቅንብር ነው።
2. ልባችን እና በእግዚአብሔር ፊት ያለው የልባችን ሁኔታ ሕይወታዊ፣ ውስጠ መሠረታዊ (intrinsically) እና ሊነጣጠል በማይችል መልኩ በእግዚአብሔር ፊት ከመንፈሳችን፣ ከነፍሳችን እና ከሥጋችን ሁኔታ ጋር የተገናኘ ነው፡-
   ሀ. የመንፈሳችን መንቀሳቀስ የሚሠራው ልባችን ንቁ ሲሆን ብቻ ነው፤ የሰው ልብ ግዴለሽ ከሆነ፣ መንፈስ በውስጥ እስረኛና አቅሙን ማሳየት የማይችል ይሆናል—ማቴ. 5፥3፣ 8፤ መዝ. 78፥8፤ ኤፌ. 3፥16-17።
   ለ. ነፍስ ሰውዬው ራሱ ነው፤ ልብ ግን ሰውዬው በድርጊት ሲገለጥ ነው፤ ልብ የመላው ማንነታችን የድርጊት ወኪል፣ የድርጊት ኮሚሽነር ነው።
   ሐ. የአካላችን ድርጊቶች እና እንቅስቃሴዎች የሚመረኮዙት በሥጋ ልባችን ላይ ነው፤ ልክ እንዲሁ የየዕለት ኑሮአችን፣ ነገሮችን የምናደርግበት እና የምንመላለስበት መንገድ የሚመረኮዘው ባለን ሥነ-ልቦናዊ ልብ ዓይነት ነው።

ለ. ልብ የሕይወት መግቢያ እና መውጫ፣ የሕይወት "ማብሪያና ማጥፊያ" ነው፤ ልብ ትክክል ካልሆነ፣ በመንፈሳችን ውስጥ ያለው ሕይወት ይከለከላል፣ የሕይወት ሕግም ወደ እያንዳንዱ የማንነታችን ክፍል ለመድረስ በነጻነት እና ሳይደናቀፍ መሥራት አይችልም፤ ሕይወት ታላቅ ኃይል ቢኖረውም፣ ይህ ታላቅ ኃይል በትንሿ ልባችን ቁጥጥር ሥር ነው—ምሳ. 4፥23፣ ማቴ. 12፥33-37፣ ተዛ. ሕዝ. 36፥26-27።

ሐ. እግዚአብሔር የማይለዋወጥ ነው፤ በተፈጥሮአዊው ውልደታችን መሠረት ግን ከሌሎች እና ከጌታ ጋር ባለን ግንኙነት ልባችን ተለዋዋጭ ነው—ተዛ. 2 ጢሞ. 4፥10፤ ማቴ. 13፥3-9፣ 18-23።

መ. በተፈጥሮአዊው፣ በስብዕና ሕይወቱ መሠረት በልቡ ጽኑ የሆነ አንድም ሰው የለም፤ ልባችን በቀላሉ ስለሚለዋወጥ፣ ፈጽሞ እምነት የሚጣልበት አይደለም—ኤር. 17፥9-10፤ 13፥23።

ሠ. ልባችን ተለዋዋጭ ስለሆነ የሚነቀፍ ነው፤ የማይለዋወጥ ልብ ነቀፋ የሌለበት ልብ ነው—መዝ. 57፥7፤ 108፥1፤ 112፥7።

ረ. በእግዚአብሔር ማዳን የልባችን መታደስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነው፤ ሆኖም፣ ልባችን ተለዋዋጭ ስለሆነ በልምምዳችን የሚታደሰው ያለማቋረጥ ነው—ሕዝ. 36፥26፤ 2 ቆሮ. 4፥16።

ሰ. ልባችን ተለዋዋጭ ስለሆነ፣ ቅዱስ በመሆን ሁኔታ፣ ለእግዚአብሔር በመለየት፣ በእግዚአብሔር በመያዝ፣ በእግዚአብሔር በመወረስ እና በእግዚአብሔር ፈጽሞ በመሞላት ሁኔታ መጽናት፣ መገንባት ይችል ዘንድ በሚቀድሰው መንፈስ ያለማቋረጥ መታደስ ያስፈልገዋል—ቲቶ 3፥5፤ 6፥19፣ 22።

ሸ. ቅዱስ የሆነን ሕይወት ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት በመኖር "[እየተቀደሱ ያሉትን]" ለመሆን፣ ልባችንን በማስተካከል ከ"ሚቀድሰው" ከእርሱ የውስጥ አሠራር ጋር መተባበር አለብን—ዕብ. 2፥11፤ መዝ. 139፥23-24፡-

1. እግዚአብሔር ልባችን ለስላሳ እንዲሆን ይፈልጋል—ሕዝ. 36፥26፤ ማቴ. 13፥4፣19፤ 2ቆሮ. 5፥14፤ ተዛ. ዘጸ. 32፥9፤ ኤር. 48፥11።
2. እግዚአብሔር ልባችን ንጹሕ እንዲሆን ይፈልጋል—ማቴ. 5፥8፤ መዝ. 73፥1፣ 25፤ ኤር. 32፥39፤ መዝ. 86፥11፤ 2 ጢሞ. 2፥22፤ 1 ጢሞ. 1፥5።
3. እግዚአብሔር ልባችን አፍቃሪ እንዲሆን ይፈልጋል—መዝ. 42፥1-2፤ መኃ. 1፥1-4፤ 2ቆሮ. 3፥16፤ 2ተሰ. 3፥5፤ ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ መዝሙር #546፣ #547፤ ኤፌ. 6፥24፤ ዮሐ. 15፥9-10፤ 21፥15-17፤ ማቴ. 26፥ 6-13፤ 1 ዮሐ. 2፥5።
4. እግዚአብሔር ልባችን በሰላም እንዲሆን ይፈልጋል—ሐዋ. 24፥16፤ 1 ዮሐ. 3፥19-21፤ ዕብ. 10፥22፤ 1 ዮሐ. 1፥7፣ 9፤ 1 ጢሞ. 1፥5፤ ፊልጵ. 4፥6-7፤ ቆላ. 3፥13-15።

ቀ. በሚቀድሰው መንፈስ የማያቋርጥ ማደስ ልባችን በቅድስና ነቀፋ የሌለው ሆኖ ሲጸና ሳለ፣ በመለኮታዊው ሕይወት አዲስነት አዲሲቱን ኢየሩሳሌምና በመለኮታዊው ባሕርይ ቅድስና ቅድስቲቱን ከተማ እየሆንን ነው—ራእ. 21፥2፤ 1 ዮሐ. 5፥11-12፤ 2 ጴጥ. 1፥4።

**II. እግዚአብሔር በፍትሃዊው ቤዛነቱ ለራሱ ይለየን ዘንድ በሚዋጀው የክርስቶስ ደም እኛን በስፍራ መቀደስ ብቻ ሳይሆን በሕይወታዊ ማዳኑ በራሱ ፈጽሞ ይሞላን ዘንድ በገዛ ቅዱስ ባሕርይው በባሕርይ እየቀደሰንም ነው—ዕብ. 13፥12፤ 10፥29፤ ሮሜ 6፥19፣ 22፤ ኤፌ. 5፥26፤ 1 ተሰ. 5፥23-24፡-**

ሀ. የእግዚአብሔር መንፈሳችንን፣ ነፍሳችንንና ሥጋችንን በባሕርይ መቀደሱ የእግዚአብሔር መገለጥ እንሆን ዘንድ በሕይወቱና በባሕርይው ተመላኪነቱን ሳይጨምር ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት እንድንሆን የእግዚአብሔር ልጆች በማድረግ መለኮታዊ በሆነ መልኩ እኛን "ልጆች ለማድረግ" ነው—ኤፌ. 1፥4-5፤ ዕብ. 2፥10-11።

ለ. እግዚአብሔር እኛን በመቀደስ፣ ሙሉ በሙሉ በባሕርይው እርሱን የምንመስል በማድረግ በመንፈሳችን፣ በነፍሳችንና በሥጋችን ውስጠ ነገረ ይለውጠናል፤ በዚህ መንገድ መንፈሳችንን፣ ነፍሳችንንና ሥጋችንን ሙሉ በሙሉ ፍጹም አድርጎ ይጠብቃቸዋል—1 ተሰ. 5፥23፡-

1. ከመጠን አኳያ፣ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ይቀድሰናል፤ ከባሕርይ ልቀት አኳያ፣ እግዚአብሔር ፍጹም አድርጎ ይጠብቀናል፣ ማለትም፣ መንፈሳችንን፣ ነፍሳችንነ እና አካላችንን [ፍጹም አድርጎ] ይጠብቃል።
2. ምንም እንኳን እግዚአብሔር ቢጠብቀንም፣ መንፈሳችንን፣ ነፍሳችንንና ሥጋችንን በመንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ መሙላት ውስጥ በማቆየት እንጠበቅ ዘንድ ከእርሱ አሠራር ጋር ለመተባበር ኃላፊነቱን፣ ተነሣሽነቱን መውሰድ አለብን—ቁ.12-24።

ሐ. መንፈሳችንን በቅድስና እንጠብቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር፣ መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ መንፈሳችንን ሕያው በሆነ ሁኔታ መጠበቅ አለብን፡-

1. መንፈሳችንን ለመጠበቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረን መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ሕያው አድርገን ልንጠብቀው ይገባል፤ በዚህ መንገድ መንፈሳችንን ካላንቀሰቀስን፣ ሙት በሆነ ሁኔታ ውስጥ እናቆየዋለን፡-
   - ሀ. መደሰት፣ መጸለይ እና ማመስገን መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ነው፤ መንፈሳችንን መጠበቅ ከሁሉ በፊት መንፈሳችንን ሕያው አድርጎ መጠበቅና ከሞት ውስጥ ጎትቶ ማውጣት ነው—ቁ. 16-18።
   - ለ. መንፈሳችንን-ሙት ከሚያደርግ ሁኔታ ለመለየት ከሚቀድሰው አምላክ ጋር መተባበር ያስፈልገናል—ተዛ. ዘኍ. 6፥6-8፤ 2 ቆሮ. 5፥4።
   - ሐ. በመንፈሳችን ውስጥ እና በመንፈሳችን እግዚአብሔርን ማምለክ፣ እግዚአብሔርን ማገልገል እና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ አለብን፤ የሆንነው ሁሉ፣ ያለን ሁሉ እና የምናደርገው ሁሉ በመንፈሳችን መሆን አለበት— ዮሐ. 4፥24፤ ሮሜ 1፥9፤ ፊልጵ. 2፥1።
2. መንፈሳችንን ለመጠበቅ፣ ከሁሉም ዓይነት እርኩሰትና ብክለት መጠበቅ ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 7፥1።
3. መንፈሳችንን ለመጠበቅ፣ በእግዚአብሔር እና በሰው ፊት ነውር የሌለበት ሕሊና ይኖረን ዘንድ መትጋት አለብን— ሐዋ. 24፥16፤ ሮሜ 9፥1፤ ተዛ. 8፥16።
4. መንፈሳችንን ለመጠበቅ፣ አእምሮአችንን በመንፈስ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ እና በመንፈሳችን ውስጥ ላለው ዕረፍት ግድ በመሰኘት ለመንፈሳችን መጠንቀቅ አለብን—ሚል. 2፥15-16፤ ሮሜ 8፥6፤ 2 ቆሮ. 2፥13።

መ. ነፍሳችንን በቅድስና እንጠብቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር፣ የሥነ-ልቦናዊውን ልባችንን ሦስት ዋና "የደም ቧንቧዎች"፣ የነፍሳችንን ክፍሎች—አእምሮአችንን፣ ስሜታችንን እና ፈቃዳችንን—ማጽዳት አለብን—ፊልጵ. 2፥2፣ 5፤ 1፥8፤ 2፥13፦

1. ነፍሳችን ትቀደስ ዘንድ፣ አእምሮአችን የክርስቶስ አእምሮ ይሆን ዘንድ መታደስ አለበት (ሮሜ 12፥2)፤ ስሜታችን በክርስቶስ ፍቅር መነካት እና ፈጽሞ መሞላት አለበት (ኤፌ. 3፥17፣19)፤ ፈቃዳችን ከሞት በተነሣው ክርስቶስ መሸነፍ እና መሰረጽ አለበት (ፊልጵ. 2፥13፤ ተዛ. መኃ. 4፥4፤ 7፥4)፤ ጌታንም በመላው ማንነታችን መውደድ አለብን (ማር. 12፥30)።
2. የሥነ-ልቦናዊ ልባችንን ሦስት ዋና ቧንቧዎችን የዘጉ ነገሮችን የምናስወግድበት መንገድ ጥልቅ ዝርዝር በሆነ መንገድ ለጌታ መናዘዝ ነው፤ በሙላት ወደ ብርሃን እንዲያመጣን ጌታን በመጠየቅ፣ ረዘም ላለ ጊዜ ከጌታ ጋር መቆየት አለብን፤ በሚያጋልጠንም ብርሃኑ፣ እንከኖቻችንን፣ ውድቀቶቻችንን፣ ሽንፈቶቻችንን፣ ስህተቶቻችንን፣ ጥፋቶቻችንን እና ኃጢአቶቻችንን መናዘዝ ያስፈልገናል—1 ዮሐ. 1፥5-9፡-
   - ሀ. የአእምሮአችንን ቧንቧ የዘጉ ነገሮችን ለማስወገድ፣ በሃሳቦቻችንን እና በአስተሳሰብ መንገዳችን ያለውን ኃጢአት የሆነውን እያንዳንዱን ነገር መናዘዝ ያስፈልገናል።
   - ለ. የስሜታችንን ቧንቧ የዘጉ ነገሮችን ለማስወገድ፣ ደስታችንን እና ኀዘናችንን የገለጥንበትን እንዲሁም በብዙ ጉዳዮችም፣ መውደድ የሚገባንን የምንጠላበትን እና መጥላት የሚገባንን የምንወድበትን ተፈጥሮአዊ ብሎም ሥጋዊ መንገድ መናዘዝ ያስፈልገናል።
   - ሐ. የፈቃዳችንን ቧንቧ የዘጉ ነገሮችን ለማስወገድ፣ በፈቃዳችን ውስጥ ያሉትን የዓመፅ ጀርሞችን መናዘዝ ያስፈልገናል።
   - መ. የሥነ ልቦናዊ ልባችንን ሦስት ዋና ቧንቧዎችን የዘጉ ነገሮችን ለማስወገድ አስፈላጊውን ጊዜ ከወሰድን፣ መላው ማንነታችን ሕያው እንደሆነና እጅግ ጤናማ በሆነ ሁኔታ እንደሆነ ስሜቱ ይኖረናል።

ሠ. ሰውነታችንን በቅድስና እንጠብቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር፣ የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ ለማከናወን የአካሉን ሕይወት በተግባር በመለማመድ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ቅዱስ ሕይወት እንኖር ዘንድ ሰውነታችንን ለእርሱ ማቅረብ አለብን—ሮሜ 12፥1-2፤ 1 ተሰ. 4፥4፤ 5፥18፦

1. የወደቀው ሰውነታችን፣ ሥጋችን የሰይጣን፣ የኃጢአት እና የሞት "መሰብሰቢያ አዳራሽ" ነው፤ ነገር ግን በክርስቶስ ቤዛነት አማካኝነት እና እንደ የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ "መሰብሰቢያ አዳራሽ" ዳግም በተወለደው መንፈሳችን፣ ሰውነታችን የክርስቶስ ብልት እና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው—ሮሜ 6፥6፣ 12፣ 14፤ 7፥11፣ 24፤ 1 ቆሮ. 6፥ 15፣ 19።
2. ሰውነታችንን መጠበቅ በሰውነታችን እግዚአብሔርን ማክበር ነው—ቁ. 20።
3. ሰውነታችንን መጠበቅ በሰውነታችን ክርስቶስን ማጉላት ነው—ፊልጵ. 1፥20።
4. ሰውነታችንን ለመጠበቅ፣ በነፍሳችን፣ በአሮጌው ሰው መሠረት መኖር የለብንም፤ ያኔ የኃጢአት ሥጋ ሥራ ይፈታል፣ ሥራ-አጥም ይሆናል—ሮሜ 6፥6።
5. ሰውነታችንን ለመጠበቅ፣ ሰውነታችንን ኃጢአት ለሆነው ለየትኛውም ነገር ማቅረብ የለብንም፤ በምትኩ፣ ራሳችንን ለጽድቅ ባሮች እና ብልቶቻችንን የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርገን ማቅረብ አለብን—ቁ. 13፣ 18-19፣ 22፤ ዳን. 5፥23፦
   - ሀ. "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ።"—1 ተሰ. 4፥3-4።
   - ለ. እግዚአብሔርን አለማወቃቸው በፍትወት ምኞት ለመዘፈቃቸው መሠረታዊው ምክንያት ነው—ቁ. 5።
6. ሰውነታችንን ለመጠበቅ፣ ቅድስቲቱን ከተማ እንሆን ዘንድ ቅዱስ አላማችንን ለመፈጸም ሰውነታችንን መጎሰም እና ባሪያ አድርገን መምራት አለብን—1 ቆሮ. 9፥27፤ ራእ. 21፥2።

**መልእክት አንድ የቡድን የንባብ ክፍል**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ተሰ. 3፥13፤ 5፥23-24

አዲስ ኪዳን፣ ስለ ንጹሕ ልብ አጽንዖት ይሰጣል። ጌታ ኢየሱስ፣ "ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና" (ማቴ. 5፥8) በማለት ተናግሯል። ጳውሎስ፣ ጢሞቴዎስን በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋር እንዲሆን መክሮታል (2 ጢሞ. 2፥22)። ከዚህም በተጨማሪ በመዝሙር 51፥10፣ ዳዊት እግዚአብሔር ንጹሕ ልብ እንዲፈጥርለት ጸልዩአል። ታድያ ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 3፥13፣ "በንጽሕና ነቀፋ የሌለበት" ከማለት ይልቅ "በቅድስና ነቀፋ የሌለበት" ያለው ለምንድን ነው? ምክንያቱ፣ የ1ኛ ተሰሎንቄ መጽሐፍ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት የተቀደሰ ሕይወት ስለ መኖር የሚናገር ስለሆነ ነው። ከምዕራፍ 1፣ 2 እና 3 የተዋቀረው የዚህ መልእክት የመጀመሪያ ክፍል መደምደሚያ፣ ጌታ ልባችንን በቅድስና ያለ ነቀፋ ማጽናቱ ነው። (Life-study of 1 Thessalonians, pp. 173- 174)

ብዙ ክርስቲያኖች የጸና ልብ ሳይሆን፣ ተለዋዋጭ፣ የማይጸና ልብ አላቸው። የሚለዋወጥ ልብ ሳይሆን በጠንካራ መንገድ የጸና ልብ ያስፈልገናል። ሆኖም፣ በተፈጥሯዊ ውልደታችን መሠረት፣ ልባችን የሚለዋወጥ ነው...ለምሳሌ፣ ማለዳ ላይ አንድ ወንድም ለሚስቱ መልካም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ቁርስ ሰዓት ላይ፣ በአንዳች ነገር ተረብሾ ጥሩ ባልሆነ መንገድ ሊያናግራት ይችላል። ይህ የልባችንን ተለዋዋጭነት በምሳሌ ያሳያል። ልባችን፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር በተገናኘ ብቻ ሳይሆን ከጌታ ጋር በተገናኘም ይለዋወጣል። እግዚአብሔር የማይለወጥ ነው፤ በፍጹም አይለወጥም። የምንለዋወጠው እኛ ነን፤ ልባችን ይለዋወጣል። በዚህ ምክንያት ጳውሎስ፣ በተሰሎንቄ ያሉት የአዲስ አማኞች ልብ መተከል፣ መታነጽ እና መጽናት አሳስቦት ነበር። (Life- study of 1 Thessalonians, p. 175)

ልብ ከሕይወት ጋር እጅግ የተዛመደ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር ሕይወቱ ከውስጣችን ተቃኝቶ እንዲወጣ ልባችንን ከማስተካከል በቀር ሌላ አማራጭ የለውም። ከእግዚአብሔር አኳያ ልባችን አራት ታላላቅ ችግሮች አለበት። እነርሱም ደንዳናነት፣ ንጹሕ አለመሆን፣ አለመውደድ እና ሰላም ማጣት ናቸው። ደንዳናነት የፈቃድ ጉዳይ ነው፤ ንጹሕ አለመሆን የአእምሮ ብቻ ሳይሆን የስሜትም ጉዳይ ነው፤ አለመውደድ የስሜት ጉዳይ ነው፣ ሰላም ማጣት ደግሞ የሕሊና ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር ልባችንን ሲያስተካክል፣ ልባችን ለስላሳ፣ ንጹሕ፣ አፍቃሪ እና በሰላም እንዲሆን እነዚህን አራት ገጽታዎች ያስተካክላል። (CWWL, 1953, vol. 3, "The Knowledge of Life," p. 110)

እግዚአብሔር ሁለንተናችንን መቀደስ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈስ፣ ነፍስና ሥጋችንን ፍጹም አድርጎ ይጠብቃል...በመጠን(quanity)፣ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ይቀድሰናል፤ በባሕርይ ልቀት(quality)፣ እግዚአብሔር መንፈሳችንን፣ ነፍሳችንን እና አካላችንን ፍጹም አድርጎ ይጠብቃል። በውድቀት፣ ሥጋችን ተበላሽቷል፤ ነፍሳችን ተበክሏል፤ መንፈሳችንም ሞቷል። በእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን፣ መላው ማንነታችን ይድናል፤ ፍጹምም ይደረጋል። ለዚህም እግዚአብሔር መንፈሳችንን ከሚገድል ከማንኛውም ንጥረ ነገር (ዕብ. 9፥14)፣ ነፍሳችንን ፍጥረታዊና አሮጌ ሆኖ ከመቅረት (ማቴ. 16፥24-26) እና ሰውነታችንንም በኃጢአት ከመበላሸት ይጠብቃል (1 ተሰ. 4፥4፤ ሮሜ 6፥6)። እንዲህ ያለው በእግዚአብሔር መጠበቅ እና የእርሱ ጥልቅ-ዝርዝር(thorough) መቀደስ፣ ጌታን በፓሮሲያው (በዳግም ምጽአቱ) እንገናኘው ዘንድ ወደ ብስለት ለመድረስ የተቀደሰ ሕይወት እንድንኖር ይደግፈናል። (Life-study of 1 Thessalonians, p. 204)

ስነ ልቦናዊው ልባችን ሦስት ዋና መተላለፊያ መንገዶች አሉት። የነፍሳችን ሦስት ክፍሎች የሆኑት እነዚህ መተላለፊያ መንገዶች፣ አእምሮ፣ ፈቃድ እና ስሜት ናቸው... የሥነ-ልቦናዊ ልባችንን ሦስት ዋና መተላለፊያ መንገዶችን የዘጉ ነገሮችን የምናስወግድበት መንገድ፣ ጥልቅ ዝርዝር በሆነ መንገድ ለጌታ በመናዘዝ ነው። እንከኖቻችንን፣ ውድቀቶቻችንን፣ ሽንፈቶቻችንን፣ ስሕተቶቻችንን፣ ጥፋቶቻችንን እና ኃጢአቶቻችንን ለመናዘዝ ለተወሰነ ጊዜ ከጌታ ጋር መቆየት እንዳለብን ከልምምዴ ተምሬያለሁ። (Life-study of 1 Thessalonians, pp. 209-210)

መልእክት ሁለት

## የዘላለማዊው ሕይወት ኅብረት— በክርስቶስ አካል የመኖር እውነታ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ዮሐ. 1፥1-2፥2

**I. የዮሐንስ መልእክቶች (በተለይ ደግሞ የመጀመሪያው መልእክቱ) የዘላለማዊውን ሕይወት ኅብረት ምሥጢር ይገልጣሉ—1 ዮሐ. 1፥3-4፤ 6-7፦**

ሀ. ኅብረት፣ እንደ ስዕል በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ በሕይወት ውኃ ፍሰት በታየው የዘላለማዊው ሕይወት በአማኞች ሁሉ ውስጥ መፍሰስ ነው፤ የክርስቶስ አካል፣ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እውነታ፣ የጌታ ኢየሱስ በውስጣችን መፍሰስ ነው፤ ይህም የሚፈሰው ማንነት በውስጣችን ፊተኛው ስፍራ ሊኖረው ይገባል—ቁ. 2-4፤ ራእ. 22፥1፤ ቆላ. 1፥18፤ ተዛ.ሕዝ. 47፥1።

ለ. ኅብረት የሚፈሰው ሦስታንዱ ነው—አብ የሕይወት ምንጭ ነው፣ ወልድ የሕይወት ፍልቅ ነው፣ መንፈስ የሕይወት ወንዝ ነው፤ ይህ ፍሰት የዘላለምን ሕይወት ጥቅል ድምር—አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ያመጣል—ዮሐ. 4፥14፤ ራእ. 22፥1-2።

ሐ. ኅብረት፣ እንደ ልዩና ብቸኛ ድርሻቸው እና በረከታቸው ዛሬ እና ለዘላለም ይደሰቱት ዘንድ የሦስታንዱ አምላክ—የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ—ወደ አማኞች ውስጥ መተላለፍ ነው—1 ቆሮ. 1፥9፤ 2 ቆሮ. 13፥14፤ ዘኁ. 6፥22-27።

መ. ኅብረት የግል ፍላጎቶችን የማስወገድ እና ከሌሎች ጋር ለሆነ የጋራ አላማ መተባበርን ያመለክታል፤ ስለዚህ፣ በመለኮታዊው ኅብረት ውስጥ መሆን የግል ፍሎጎቶቻችንን ወደ ጎን መተው እና ለእግዚአብሔር አላማ መከናወን ከሐዋርያት እና ከሦስታንዱ አምላክ ጋር መተባበር ነው—ሐዋ. 2፥42፤ 1 ዮሐ. 1፥3።

ሠ. ኅብረት ከትምህርት ይመጣል፤ በተሳሳተ እና ከሐዋርያት ትምህርት፣ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትምህርት በተለየ መንገድ ካስተማርን፣ ትምህርታችን ቡድናዊ፣ ከፋፋይ ኅብረትን ያፈራል—ሐዋ. 2፥42፤ 1 ጢሞ. 1፥3-6፤ 6፥3-4፤ 2 ቆሮ. 3፥8- 9፤ 5፥18።

ረ. አንደኛ ዮሐንስ የመለኮታዊውን ኅብረት መርሆች ይገልጣል፤ 2ኛ ዮሐንስ ክርስቶስን ከሚክዱ ጋር ምንም ዓይነት ኅብረት ማድረግ እንደሌለብን ይገልጣል (ቁ. 7-11)፤ 3ኛ ዮሐንስ፣ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ለወንጌል እና ለቃሉ አገልግሎት የሚጓዙትን በመላክ እና በቤተ ክርስቲያን ዋና መሆንን ባለመውደድ (ቁ. 5-10) በእግዚአብሔር ቤተሰብ አንዱ ኅብረት ውስጥ መቆየት እንዳለብን ይገልጣል።

**II. የዘላለማዊው ሕይወት ኅብረት በመንፈስ አንድነት በክርስቶስ አካል ውስጥ የመኖር እውነታ ነው—1 ቆሮ. 10፥16-18፤ ሐዋ. 2፥42፤ ኤፌ. 4፥3፦**

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ወደሚደረግ የመለኮታዊው ኅብረት ገጽታ የምንገባው በመለኮታዊው መንፈስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ነው፤ ይህ የኅብረት ገጽታ ሦስታንዱን አምላክ በመውደዳችን ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል—2 ቆሮ. 13፥14፤ 1 ዮሐ. 1፥3፤ 1 ዮሐ. 1፥3፣ 6፤ ማር. 12፥30።

ለ. እርስ በርስ ወዳለን የመለኮታዊው ኅብረት የምንገባው በሰው መንፈሳችን ነው፤ ይህ የኅብረት ገጽታ፣ መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ እርስ በርስ ባለን በመዋደድ አንዳችን ከሌላችን ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል—ፊልጵ. 2፥1፤ ራእ. 1፥10፤ 1 ዮሐ. 1፥2-3፣ 7፤ 1 ቆሮ. 16፥18፤ ማር. 12፥31፤ ሮሜ 13፥ 8-10፤ ገላ. 5፥13-15።

ሐ. አንዱ መለኮታዊ ኅብረት የተሸመነ ኅብረት ነው—ወደ ጎን የሆነው የእርስ በርስ ኅብረት ወደ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ከሆነው ኅብረት ጋር ተሸምኗል፦

1. የሐዋርያት የመጀመሪያው ልምምድ ከአብ እና ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደላይ የነበረው ኅብረት ነበር፤ ነገር ግን ሐዋርያት የዘላለምን ሕይወት ለሌሎች ሲዘግቡ፣ ወደ ጎን የእርስ በርስ የነበረውን የመለኮታዊውን ኅብረት ገጽታ ተለማመዱ—1 ዮሐ. 1፥2-3፤ ተዛ. ሐዋ. 2፥42።
2. እርስ በርስ ከቅዱሳን ጋር ያለን ወደ ጎን የሆነው ኅብረታችን ከጌታ ጋር ወደምናደርገው ወደ ላይ ወደ ሆነው ኅብረት ውስጥ ያመጣናል፤ ያኔ ወደ ላይ ከጌታ ጋር የምናደርገው ኅብረት ከቅዱሳን ጋር ወደ ጎን ወደምናደርገው ኅብረት ያመጣናል።
3. በመንፈሳዊው ገጽታ ጤናማ እንሆን ዘንድ ወደ ላይ እና ወደ ጎን የምናደርጋቸውን የመለኮታዊውን ኅብረት ገጽታዎች መጠበቅ አለብን—ተዛ. 1 ዮሐ. 1፥7፣ 9።

መ. መለኮታዊው ኅብረት በክርስትና ሕይወታችን ሁሉ ነገር ነው፦

1. ኅብረት ሲጠፋ እግዚአብሔርም ይጠፋል፤ እግዚአብሔር የሚመጣው እንደ ኅብረት ነው—2 ቆሮ. 13፥14፤ ራእ. 22፥1።
2. በዚህ መለኮታዊ ኅብረት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሸመናል፤ ይህ መሸመን፣ በሕይወት ለማደጋችን እና ለመለወጣችን መለኮታዊውን ቅንብር ወደ መንፈሳዊው ማንነታችን ውስጥ ለማምጣት የእግዚአብሔር እና የሰው መዋሐድ ነው—ዘሌ. 2፥4-5።
3. መለኮታዊው ኅብረት ወደ አንድ አካል በአንድ ላይ ያገጣጥመናል፣ ያርቀናል፣ ያስተካክለናል፣ በኅብር ያደርገናል፣ ያዋሕደንማል—1 ቆሮ. 10፥16-18፤ 12፥24-25።

**III. በመለኮታዊው ኅብረት ድሰታ(enjoyment) ውስጥ ለመቆየት፣ በባሕርያችን ውስጥ ላለው ኃጢአት ክርስቶስን እንደ የኃጢአት መሥዋዕታችን፣ በምልልሳችን ኃጢአት ላለባቸው ድርጊቶቻችን ደግሞ እንደ የበደል መሥዋዕታችን መውሰድ ያስፈልገናል—1 ዮሐ. 1፥8-9፤ 3፥20-21፤ ዘሌ. 4፥3፤ 5፥6፤ ዮሐ. 1፥29፤ ሮሜ. 8፥3፤ 2 ቆሮ. 5፥21፤ 1 ጴጥ. 2፥24-25፦**

ሀ. ኃጢአት፣ በአዳም ውድቀት በኩል ወደ ሰው ውስጥ ራሱን የከተተው እና አሁን በወደቀው ሰው ውስጥ እንደ ሕግ የሚኖረው፣ የሚንቀሳቀሰው እና የሚሠራው የዓመፅ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ የሆነው፣ የሰይጣን ክፉ ተፈጥሮ ነው—ሮሜ 5፥12፣ 19፣ 21፤ 6፥14፤ 7፥11፣ 14፣ 17-23፤ መዝ. 51፥5፤ 1 ዮሐ. 3፥4;፤ ተዛ. 2 ተሰ. 2፥3፣7-8።

ለ. ክርስቶስን እንደ የኃጢአት መሥዋዕት መውሰድ ማለት፣ አሮጌው ሰዋችንን ተወግዷል (ሮሜ 6፥6)፣ በወደቀው ሰው ውስጥ ያለው ኃጢአት ተወግዷል (ሮሜ 8፥3)፤ ኃጢአትን ራሱ የሆነው ሰይጣን ተደምስሷል (ዕብ. 2፥14)፣ ዓለም ተፈርዶበታል እና የዚህ ዓለም ገዢ ተጥሏል (ዮሐ. 12፥31) ማለት ነው፦

1. "የዚህ ዓለም ገዢ" በሚለው ሃረግ ውስጥ "ገዢ" የሚለው ቃል ሥልጣንን ወይም ኃይልንን እና ለሥልጣን የሚደረገውን ሽኩቻ ያመለክታል—ሉቃ. 4፥5-8፤ ተዛ. ማቴ. 20፥20-21፣ 24፤ 3 ዮሐ. 9።
2. ለሥልጣን የሚደረግ ሽኩቻ የሥጋ፣ የኃጢአት፣ የሰይጣን፣ የዓለም እና የዚህ ዓለም ገዢ ውጤት ነው—ገላ. 5፥16-17፣ 24-26።
3. በሥጋችን ያለው የኃጢአት ሕግ እግዚአብሔርን በመጻረር ከእርሱ ጋር ለመታገል ቅጽበታዊ ኃይል፣ ጥንካሬ እና ጉልበት ነው፤ የኃጢአት መሥዋዕት ሕግ፣ ከሰው ቁጥጥር ውጪ እና በቅጽበት ከኃጢአት ሕግ አርነት ያወጣን ዘንድ የምንደሰተው የእስትንፋሳዊው ክርስቶስ የሕይወት ሕግ ነው—ሮሜ 7፥23፤ 8፥2፤ ዘሌ. 6፥24-30፤ ተዛ. 7፥1-10።

ሐ. የእግዚአብሔር ሕዝብ በመንፈስ አንድነት ይጠበቁ ዘንድ፣ ክርስቶስን ኃጢአትን እንደሚያስወግድ ሕይወት ለእነርሱ በማገልገል ችግሮቻቸውን መሸከም እንድንችል፣ እርሱን እንደ ሕይወታችን፣ የሌሎችን ኃጢአቶች እንደሚሸከም ሕይወታችን በመደሰታችን ግንዛቤ ክርስቶስን እንደ የኃጢአት መሥዋዕታችን እንካፈለዋለን—1 ዮሐ. 5፥16፤ ዘሌ. 10፥ 17።

መ. ብርሃን ከሆነው እግዚአብሔር (1 ዮሐ. 1፥5፤ ቆላ. 1፥12) ጋር በምናደርገው እውነተኛ፣ የቅርብ፣ ሕያው እና በፍቅር የተሞላ በሆነው ኅብረታችን በኩል፣ ኃጢአተኛ እንደሆንን እንገነዘባለን፣ ክርስቶስን እንደ የኃጢአት እና የበደል መሥዋዕታችን እንወስደውማለን፡-

1. ጌታን ይበልጥ በወደድነው እና በተደሰትነው መጠን፣ ምን ያህል ክፉ እንደሆንን ይበልጥ እናውቃለን—ኢሳ. 6፥5፤ ሉቃ. 5፥8፤ ሮሜ 7፥18።
2. ኃጢአተኛ ተፈጥሮ እንዳለን መገንዘባችን እና ክርስቶስን እንደ የኃጢአት መሥዋዕታችን መውሰዳችን እንድንፈረድ እና እንድንገዛ ያደርገናል፤ ይህም ግንዛቤ ይጠብቀናል፣ ምክንያቱም ምንም ዓይነት በራስ መተማመን እንዳይኖረን ያደርገናልና—ፊልጵ. 3፥3፤ ተዛ. ዘጸ. 4፥6።
3. እግዚአብሔርን ለመግለጥ እና ለመወከል አላማ በእግዚአብሔር የተፈጠረው ሰው ከእግዚአብሔር ውጭ ለምንም ነገር መሆን የለበትም፣ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መሆን አለበት፤ ስለዚህ፣ መልካምም ይሁን ክፉ ከራሳችን የምናደርገው የትኛውም ነገር ለራሳችን ነው፣ ለራሳችን እንጂ ለእግዚአብሔር ስላልሆነም፣ በእግዚአብሔር ዓይን በኃጢአት የተሞላ ነው፤ ኃጢአት ለራስ መሆን ነው—ዘፍ. 1፥26፤ ኢሳ. 43፥7፤ ሮሜ 3፥23።
   ሀ. ለራሳችን ስንል ጌታን ማገልገል ኃጢአት ነው፤ ራሳችንን መስበክ ኃጢአት ነው—ዘኊ. 28፥2፤ 2 ነገ. 5፥20-27፤ ማቴ. 7፥22-23፤ 2 ቆሮ. 4፥5።
   ለ. ራሳችንን ለመግለጥ እና ለማሳየት፣ እንደ ምጽዋት መስጠት፣ ጸሎት እና ጾም ያሉ የራሳችንን ጻድቅ ድርጊቶች ለራሳችን ማድረግ ኃጢአት ነው —ማቴ. 6፥1-6።
   ሐ. ለራሳችን (ስም፣ ሥልጣን፣ ጥቅም እና ትምክህት) ሌሎችን መውደድ ኃጢአት ነው፤ ልጆቻችንን ለራሳችን እና ለወደፊታችን አስበን ማሳደግ ኃጢአት ነው—ሉቃ. 14፥12-14፤ ተዛ. 1 ቆሮ. 7፥14።
4. ጌታ ከእኔነት የሆነውን ነገር ሁሉ እንድንተው እና በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ እንድንደገፍ ምን ያህል አስቃቂ፣ አስከፊ እና አጸያፊ እንደሆንን ያሳየን ዘንድ ውድቀቶቻችንን ይጠቀማል—መዝ. 51፤ ሉቃ. 22፥31-32፤ ሮሜ 8፥28።

ሠ. ክርስቶስን እንደ የበደል መሥዋዕት እውነታ መውሰድ፣ እርሱን በሕይወት ኅብረት እንደ የሕይወት አቅርቦት እንደሰተው ዘንድ፣ እርሱን እንደሚዋጀው ማንነት፣ እንደሚያበራው ማንነት እና እንደሚገዛው ማንነት መለማመድ ነው—1 ዮሐ. 1፥ 1—2፥2፤ ራእ. 21፥21፣ 23፤ 22፥1-2፡-

1. ክርስቶስን እንደ የበደል መሥዋዕት ስንወስድ፣ በጎ እና ንጹሕ ሕሊና ይኖረን ዘንድ ኃጢአቶቻችንን እና የረከሰንባቸውን ነገሮች ሁሉ በዝርዝር መናዘዝ ያስፈልገናል—ሐዋ. 24፥16፤ 1 ጢሞ. 1፥5፣ 19፤ 3፥9፤ 2 ጢሞ. 1፥3፤ ዕብ. 9፥14፤ 10፥22።
2. ኃጢአቶቻችንን ብንናዘዝ፣ እግዚአብሔር ይቅር ሊለን በቃሉ የታመነ እና ከዓመፃ ሁሉ ሊያነጻን በቤዛነቱ ጻድቅ ነው፤ በተጨማሪም፣ በመለኮታዊው ኅብረት ድሰታ እንኖር ዘንድ ከአብ ጋር የተቋረጠውን ኅብረታችንን ለመመለስ ታላቅ ወንድማችን ክርስቶስ በአብ ዘንድ ያለ ጠበቃችን ነው—1 ዮሐ. 1፥7፣ 9፤ 2፥1-2።
3. የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ደም ማንጻት ከእግዚአብሔር የመለየትን ችግር፣ በሕሊናችን ውስጥ ያለውን የጸጸት ችግር እና ከሰይጣን የሚመጣውን የክሶች ችግር ይፈታል፣ ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር መገኘት የተሞላ የዕለት ተዕለት ሕይወት እንዲኖረን ያስችለናል—መዝ. 103፥1-4፣ 12-13፤ 32፥1-2፤ ራእ. 12፥10-11።
4. በመለኮታዊው ብርሃን ኃጢአቶቻችንን በመናዘዝ ክርስቶስን እንደ የበደል መሥዋዕታችን መውሰድ፣ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም እንሆን ዘንድ ክርስቶስን እንደ ሕያው ውኃ የመጠጣት መንገድ ነው—ዮሐ. 4፥14-18።
5. ለኃጢአቶቻችን ይቅርታ ለመቀበል ክርስቶስን እንደ የበደል መሥዋዕታችን መውሰድ እግዚአብሔርን መፍራታችንን እና እግዚአብሔርን መውደዳችንን ያመጣል —መዝ. 130፥4፤ ሉቃ. 7፥47-50።

**IV. በመለኮታዊው ኅብረት ክርስቶስን ስንደሰት ሳለን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ያሉ አራት ወሳኝ የሆኑ ነገሮችን ዑደት ባለማቋረጥ እንለማመዳለን—ዘላለማዊው ሕይወት፣ የዘላለማዊው ሕይወት ኅብረት፣ መለኮታዊው ብርሃን እና የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ደም፤ እንዲህ ዓይነቱ ዑደት፣ ሙሉ ሰው እንሆን ዘንድ፣ ወደ ክርስቶስ ሙላቱ ልክ ደርሰን እንሞላ ዘንድ ወደ ሕይወት ብስለት በጋራ እስክንደርስ ድረስ በመለኮታዊው ሕይወት እድገት ወደፊት እንድንገፋ ያደርገናል—1 ዮሐ. 1፥1-9፤ ዕብ. 6፥1፤ ኤፌ. 4፥13።**

**መልእክት ሁለት የቡድን የንባብ ክፍል**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ዮሐ. 1፥1-2፥2

ኅብረት ለሚለው ቃል የግሪኩ አቻ ኮይኖኒያ ሲሆን፣ ትርጉሙም "የጣምራ ተሳትፎ፣ የጋራ ተሳትፎ" የሚል ነው። ኅብረት የዘላለማዊው ሕይወት ውጤት እና በእርግጥም መለኮታዊውን ሕይወት በተቀበሉና የራሳቸው ባደረጉት አማኞች ሁሉ ውስጥ ያለው የመለኮታዊው ሕይወት ፍሰት ነው። በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ባለው የሕይወት ውኃ ፍሰትም ተመስሏል (ራእ. 22፥1)። በመሆኑም፣ ሁሉም እውነተኛ አማኞች በዚህ ኅብረት ውስጥ ናቸው (ሐዋ. 2፥42)። ይህ የሚከናወነው ዳግም በተወለደው መንፈሳችን ውስጥ ባለው መንፈስ አማካኝነት ነው። በዚህም ምክንያት፣ "የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት" (2 ቆሮ. 13፥14) እና "የእኛ መንፈስ ኅብረት" (ፊልጵ. 2፥1) ተብሎ ይጠራል። እኛ አማኞች፣ አብ እና ወልድ በሆኑትና ለእኛ ባከናወኑት ሁሉ ውስጥ የምንሳተፈው በዚህ የዘላለማዊው ሕይወት ኅብረት ነው፤ ይህም የአብን ፍቅር እና የወልድን ጸጋ በመንፈስ ኅብረት አማካኝነት በመደሰታችን በኩል ነው። እንዲህ ያለው ኅብረት፣ አብን እና ወልድን በመንፈስ አማካኝነት በመደሰታቸው አስቀድሞ የሐዋርያት እድል ፈንታ ነበር። ስለሆነም፣ በሐዋርያት ሥራ 2፥42 "የሐዋርያት ኅብረት" እና በ1ኛ ዮሐንስ 1፥3 ደግሞ "ኅብረታችንም" (የሐዋርያቱ ኅብረት)፣ ከአብ ጋር እና ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለ ኅብረት ተብሎ ተጠርቷል።

ኅብረት ማድረግ በአንድ ነገር ላይ የጋራ ተሳትፎ ማድረግ ነው።...መለኮታዊው ሕይወት፣ ሕይወታዊ፣ ብልጡግ፣ የሚንቀሳቀስ እና ንቁ ስለሆነ፣ ልዩ የሆነ ውጤት፣ አንዳች የሚያስከትለው ነገር አለ። የመለኮታዊው ሕይወት ውጤት፣ የሚያስከትለው ነገር፣ የሕይወት ኅብረት ነው።

የመለኮታዊው ሕይወት ኅብረት በራእይ 22፥1 ላይ በግልጽ ታይቷል። ከዚህ ጥቅስ፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር እና ከበጉ ዙፋን የሚፈስን የሕይወት ውኃ ወንዝ እናያለን። የእግዚአብሔር እና የበጉ ዙፋን፣ የሚቤዠው እግዚአብሔር፣ የበጉ-እግዚአብሔር ዙፋን ነው። በዘፍጥረት ፈጣሪውን እግዚአብሔር እናገኛለን፤ በራእይ መጽሐፍ ላይ ግን የሚቤዠውን እግዚአብሔር እናገኛለን። ከዚህ ከሚቤዠው እግዚአብሔር እንደ ምንጭ፣ የሕይወት ውኃ ወንዝ ይፈሳል። የሕይወት ውኃ ወንዝ ፍሰት የሕይወት ኅብረት ነው። ይህ ማለት፣ ያ ኅብረት ከሚቤዠው እግዚአብሔር ውስጥ የሚወጣ የመለኮታዊው ሕይወት ፍሰት ነው።

በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ባለው ሥዕል መሠረት፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ያለው ወንዝ የከተማይቱ አሥራ ሁለት በሮች ጋር እስኪደርስ ድረስ ቁልቁል እየተሽከረከረ የሚፈስ ነው። በዚህም መላው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተማ በዚህ ሕያው ውኃ ፍሰት አቅርቦት እንደምታገኝ ማየት እንችላለን፤ ይህም በሕይወት ኅብረት አማካኝነት አቅርቦትን ታገኛለች ማለት ነው። የመለኮታዊው ሕይወት ኅብረት፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሆና የምትጠናቀቀውን የክርስቶስ አካል እያንዳንዱን ብልት ለመድረስ ከእግዚአብሔር በመውጣት፣ በሕዝቡ በኩል ይፈስሳል።

የመለኮታዊው ሕይወት ኅብረት ወይም የመለኮታዊው ሕይወት ፍሰት፣ የመንፈስ ኅብረት ነው። 2ኛ ቆሮንቶስ 13፥14 "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን" ይላል። እዚህ ጋር የእግዚአብሔር አብ ፍቅር ምንጭ እንደሆነ፣ የክርስቶስ ጸጋ ፍልቅ እንደሆነ እና የመንፈስ ኅብረት የፍልቁ መፍሰስ እንደሆነ እናያለን። የክርስቶስን ጸጋ እና የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ለድሰታችን ወደ እኛ የሚያመጣው ይህ ፍሰት ነው።

በመለኮታዊው ሕይወት ኅብረት ውስጥ ለእግዚአብሔር ዓላማ መከናወን ከሐዋርያት እና ከሦስታንዱ አምላክ ጋር እንተባበራለን። በ1ኛ ዮሐንስ 1፥3 ያለው የዮሐንስ ቃል፣ የግል ፍላጎቶችን ወደ ጎን የማድረግ እና ለአንድ የጋራ ለሆነ ዓላማ ከሌሎች ጋር መተባበርን ያመለክታል። በመሆኑም፣ ከሐዋርያት ጋር ኅብረት ማድረግ፣ በሐዋርያት ኅብረት ውስጥ መሆን እና በሐዋርያት ኅብረት ውስጥ ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ኅብረት ማድረግ፣ የግል ፍሎጎቶቻችንን ወደ ጎን ማድረግ እና ለእግዚአብሔር ዓላማ መከናወን ከሐዋርያት እና ከሦስታንዱ አምላክ ጋር መተባበር ነው። (Life-study of 1 John, pp. 40-41, 46)

የመለኮታዊው ሕይወት ኅብረት ወደ ላይ እና ወደ ጎን የሆነ ገጽታ አለው። ወደ ላይ የሆነው የኅብረት ገጽታ ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል። ወደ ጎን የሆነው የኅብረት ገጽታ አንዳችን ከሌላችን ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል።

ወደ ላይ የሆነው የኅብረት ገጽታ በመጀመሪያ የተመሠረተው በቀዳሚዎቹ ሐዋርያት ነው። ሐዋርያቱ በመቀጠል፣ ኃጢአተኞች ሐዋርያቱ ጋር ኅብረት ይኖራቸው ዘንድ የዘላለምን ሕይወት ዘገቡላቸው። ሐዋርያት ራሳቸው የዘላለምን ሕይወት ለእነርሱ ከመዘገባቸው በፊት፣ አስቀድሞውኑ ከአብ ጋር እና ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር (1 ዮሐ. 1፥3) ወደ ላይ የሆነው ኅብረት ነበራቸው።...ሐዋርያት የዘላለምን ሕይወት ለሌሎች ሲዘግቡ፣ ወደ ጎን የሆነውን የመለኮታዊውን ኅብረት ገጽታ ተለማመዱ።

የመለኮታዊው ኅብረት ሁለቱም ገጽታዎች በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፤ ስለዚህም የትኛው ገጽታ አስቀድሞ እንደሚመጣ መናገር አስቸጋሪ ነው። ከጌታ ጋር ተገቢ ኅብረት ከሌላችሁ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ አስቸጋሪ ነው። በተመሳሳይ መንገድ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ተገቢ ኅብረት ከሌላችሁ፣ ከጌታ ጋር ኅብረት ማድረግ አስቸጋሪ ነው።

መንፈስ ከኅብረት ጋር የተቆራኘ፣ በኅብረት የተሸፈነ እና ከኅብረት ጋር የተዋሐደ ብቻ አይደለም። መንፈስ ራሱ ኅብረት ነው፤ ምክንያቱም ኅብረት የመንፈስ ፍሰት፣ ጅረት ነው። ይህ፣ የኤሌክትሪክ ጅረት ኤሌክትሪኩ ራሱ ነው እንደማለት ነው። የኤሌክትሪኩ ጅረት፣ ኤሌክትሪክ በእንቅስቃሴ ላይ ሲሆን ነው። ኤሌክትሪኩ ሲቆም የኤሌክትሪኩ ፍሰትም ይቆማል። በተመሳሳይ መንገድ፣ በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፥14 ላይ የተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ ኅብረትም የመንፈስ መንቀሳቀስ ነው። የክርስቶስ ፍቅር፣ ክርስቶስን ራሱን እኛ ስንደሰተው ነው፤ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ እግዚአብሔርን ራሱን እኛ ስንቀምሰው ነው፤ የመንፈስ ኅብረት ደግሞ መንፈስ ራሱ በውስጣችን ሲንቀሳቀስ ነው። መለኮታዊው ኅብረት መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው።

በሰው መንፈሳችን አማካኝነት ወደ ጎን ወደ ሆነው የመለኮታዊው ኅብረት ገጽታ መግባት ያስፈልገናል (ፊልጵ. 2፥1፤ ራእ. 1፥10) ። አንዳችን ከሌላችን ጋር ወደ ጎን የሆነው እውነተኛ ኅብረት እንዲኖረን ከፈለግን፣ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ አለብን። መንፈሳችንን ካንቀሳቀስን፣ ፈጽሞ ዓለማዊ በሆነ መንገድ አናወራም ወይም ደግሞ ቅዱሳንን ወይም አብያተ ክርስቲያናትን በተመለከተ አሉታዊ ንግግር መናገር አንችልም።...እንዲህ ዓይነቶቹ ውይይቶች በቅዱሳን መካከል ሐሜትንና ሞትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያዛምታሉ። በቅዱሳን መካከል ያለው እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት የመንፈስ ኅብረት አይደለም።... በፊልጵስዩስ 2፥1-2 ጳውሎስ እንዲህ እያለ ይመስላል፦ “ወንድሞች፣ ከእኔ ጋር አንዳች ኅብረት በመንፈስ ካላችሁ፣ ኅብረታችሁ ለእኔ መበረታታት እና መጽናናት ይሆንልኛል። ከዚያም ደስታዬን ፍጹም ታደርጉልኛላችሁ።”

ወደ ጎን እና ወደ ላይ የሆኑት የኅብረት ገጽታዎች እጅግ በቅርበት የተቆራኙ ናቸው። ይህንን ከልምምዳችን ማየት እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ስለ ሁኔታቸው ኅብረት ለማድረግ በሚል ጭምብል ስለ ሌሎች ቅዱሳን ልናወራ እንችላለን፤ በእውነቱ ግን ንግግራችን ሐሜት ነው። ከዚያ በኋላ ግን መጸለይ ያቅተናል ምክንያቱም መንፈሳችን በሐሜታችን ምክንያት ተዳፍኗል። ነገር ግን መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ እውነተኛ በሆነ መንገድ ኅብረት ስናደርግ፣ ለመጸለይ እና ጌታን ለመንካት እንጓጓለን። ይህ፣ ወደ ላይ እና ወደ ጎን በሆኑት የኅብረት ገጽታዎች መካከል ያለው ግንኙነት እንዴት የተቀራረበ እደሆነ ያሳያል።...ሁለት ወንድሞች እውነተኛ፣ ተገቢ፣ ወደ ጎን የሆነ ኅብረት እንዲኖራቸው መንፈሳቸውን ካንቀሳቀሱ፣ በስተመጨረሻ እጅግ እውነተኛ እና ከልብ ወደ ሆነ ምልጃ ውስጥ ይገባሉ። አንድ ላይ በሚጸልዩበት ጊዜ፣ የመለኮታዊው ኅብረት ሁለቱ ገጽታዎች አብረው ይሸመናሉ።...ይህ የተሸመነ ኅብረት እውነተኛው ኅብረት ነው።

መለኮታዊው ኅብረት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሁሉንም ነገር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የኖረው በዚህ ኅብረት ውስጥ ነው። በመለኮታዊው ኅብረት ውስጥ ስንኖር፣ የክርስትና ሕይወታችን እጅግ ሕያው፣ ንቁ እና ተጽእኖ ያለው ይሆናል። (CWWL, 1990, vol. 1, “The Triune God to Be Life to the Tripartite Man,” pp. 354-365)

በ1ኛ ዮሐንስ 1፥1-7 በመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚገኙ የአራት ወሳኝ ነገሮችን ዑደት እናያለን—የዘላለማዊው ሕይወት፣ የዘላለማዊው ሕይወት ኅብረት፣ መለኮታዊው ብርሃን እና የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ደም።...ዘላለማዊው ሕይወት ይበልጥ ሲኖረን፣ የዚህን ሕይወት ኅብረት ይበልጥ ወደ እኛ ያመጣል። የመለኮታዊውን ሕይወት ኅብረት ይበልጥ ስንደሰት፣ መለኮታዊውን ብርሃን ይበልጥ እንቀበላለን። መለኮታዊውን ብርሃን ይበልጥ ስንቀበል፣ በኢየሱስ ደም ማንጻት ውስጥ ይበልጥ እንሳተፋለን። እንዲህ ያለው ዑደት ወደ ሕይወት ብስለት እስክንደርስ ድረስ በመለኮታዊው ሕይወት እድገት ወደ ፊት ይወስደናል።

በኅብረት ውስጥ በመለኮታዊው ብርሃን ስር በምንሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ወይም ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ስህተት እንደሆንን ሲሰማን፣ ወዲያውኑ ኃጢአታችንን ለጻድቁ አባታችን መናዘዝ አለብን። አባታችን ይቅር ሊለን ዝግጁ ነው።... አንዴ ኃጢአታችንን ከተናዘዝን አባታችን ታማኙ እና ጻድቁ አምላክ ይሆንልናል (1 ዮሐ. 1፥9)። ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን እና የበደላችንን እድፍ ሊያጥብልን እየጠበቀ ነው።

ዮሐንስ ለትንንሽ ልጆቹ፣ እነርሱም የዚህ መልእክት ተቀባዮች ለሆኑት ሁሉ፣ ይህን መልእክት የጻፈበት ውጥን ኃጢአት እንዳያደርጉ እንደሆነ ይነግራቸዋል (2፥1)። ነገር ግን ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ፣ ከአብ ዘንድ ጠበቃ፣ ረዳት ወይም መካር አለን፤ እርሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

መለኮታዊውን ሕይወት ተቀብለናል፤ በሕይወት ኅብረትም ይህንን ሕይወት እየተደሰትነው ነው። በዚህ ኅብረት መለኮታዊውን ብርሃን እንቀበላለን፤ በዚህም ብርሃን እውነትን እንለማመዳለን። ነገር ግን አሁንም በሥጋችን ስለሚያድረው ኃጢአት ማስጠንቀቂያ ያስፈልገናል።

ኃጢአትን በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ፣ ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር መናዘዝ ያስፈልገናል። በኃጢአታችን ብንናዘዝ፣ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን በቃሉ የታመነ ነው፤ ከዓመፃችን ሁሉ ሊያነጻንም በቤዛነቱ ጻድቅ ነው (1፥9)።...ሆኖም 2፥1-2 እንደሚያመለክተው፣ አሁንም ለጉዳያችን አንድ ማንነት፣ በአብ ዘንድ ያለ ጠበቃ ያስፈልገናል። እኛ ራሳችን ጉዳዩን ለማስፈጸም ብቁ ስላልሆንን ሰማያዊ ጠበቃ ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር፣ ይቅር እንድንባልና እንድንነጻ ስለ እኛ የፈሰሰውን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ብቻ ሳይሆን ያዘጋጀው፣ ክርስቶስንም እንደ ጠበቃችን አዘጋጅቶልናል። በመጀመሪያ፣ ጌታ ኢየሱስ እንደ የቤዛነታችን ዋጋ ደሙን አፍስሷል። ደሙን ካፈሰሰም በኋላ፣ ስለ እኛ የሚቆም ጠበቃችን፣ ሰማያዊ ጠበቃችን ሆኗል።

ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሳይሆን ከአብ ዘንድ ያለ ጠበቃችን የመሆኑ ሃቅ፣ ጌታ ስለ እኛ የሚቆምበት ጉዳይ የቤተሰብ ጉዳይ መሆኑን፣ እንደ የአብ ልጆች በእኛ እና በአብ መካከል ያለ ጉዳይ መሆኑን ያመለክታል። በእውነቱ፣ ጠበቃችን ታላቅ ወንድማችን፣ የአብ ልጅ ነው።

መለኮታዊው ቤተሰብ በፍቅር የተሞላ ነው፤ ደግሞም ግን በጽድቅ የተሞላ ነው። በመሆኑም ደንቦች እና የአባት ተግሣጾች አሉት።...አባታችን ሥርዓት ያለው ነው፤ ቤቱም ከሰውኛው ፍርድ ቤት ይልቅ እጅግ ሥርዓት ያለው መሆን አለበት። ይሁን እንጂ፣ በአብ ቤት ውስጥ እንዳሉ ልጆች አብዛኛውን ጊዜ አስቸጋሪዎች ነን። እንሳሳታለን፤ የቤተሰቡን ደንብ እንሽራለን፤ አብንም እናስከፋለን። በዚህ ምክንያት፣ ጌታ ታላቅ ወንድማችን፣ ከአብ ዘንድ ያለ ጠበቃችን እንዲሆንልን ያስፈልገናል። ስለ እኛ ደሙን እንዳፈሰሰው ማንነት፣ ጌታ ኢየሱስ ጻድቅ የሆነው ነው። እርሱ ከአብ ጋር ብቻ ሳይሆን ከእኛም ጋር ትክክል ነው። ጌታ የእኛ ጳራቅሊጦስ ነው (ይህም የግሪክ ቃል “ጠበቃ” ተብሎ ተተርጉሟል)። እኛን ለመርዳት ከጎናችን ይቆማል፤ ያገለግለናል፤ ይንከባከበናል፤ የሚያስፈልገንን ሁሉም ይሰጠናል። የሚያነጻው ደም ያስፈልገን ነበር፤ ስለዚህም ለቤዛነታችንና ለመንጻታችን የገዛ ደሙን ሰጠን። ጉዳያችንን የሚከታተል ሰውም ያስፈልገናል። ስለዚህም፣ እርሱ አሁን ጠበቃችን፣ የእኛ ጳራቅሊጦስ ነው። (Life-study of 1 John, pp. 68, 120-121, 117-119)

## መልእክት ሦስት

## ለእውነተኛው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የክርስቶስ የላቀ ውድነት

## ራእይ፣ ልምምድ፣ ድሰታ እና መገለጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ጴጥ. 1፥7፣ 19፤ 2፥4፣ 6-7፤ 3፥4፤ 2 ጴጥ. 1፥1፣ 4

**I. በክርስቶስ ያመኑ አማኞች በዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳባቸው ለውጥ ሊኖራቸው ይገባል——ማቴ. 23፥16-26፤ 1 ሳሙ. 16፥7፤ ሉቃ. 16፥15፤ 9፥54-56፤ 1 ጴጥ. 3፥4፤ ፊልጵ. 3፥7-8፡-**

ሀ. ለአማኞች ተገቢ የሆነው የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳብ በሚከተሉት ለክርስቶስ እና ለሙሉ ማዳኑ ገጽታዎች በሚሰጡት ግምታቸው እና ግምገማቸው ሊታይ ይችላል፦

1. ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ ጌታ ኢየሱስ የማዕዘን ራስ ስለመሆኑ የሚሰጡት ግምት——መዝ. 118፥22፤ 1 ጴጥ. 2፥7።
2. ከዘመዶቻቸው ጋር ሲነጻጸር ለጌታ ኢየሱስ የሚሰጡት ግምት——ማቴ. 10፥37-38፤ ሉቃ. 18፥26-30፤ 1 ጴጥ. 1፥1፣ 17፤ 2፥11።
3. ከምድራዊ ሀብት ጋር ሲነጻጸር ጌታ ኢየሱስ የፍትሕ መዝገብ ስለመሆኑ የሚሰጡት ግምት—ኢዮ. 22፥23-28፤ ማቴ.12፥18-21፤ ኢሳ. 42፥1-4፤ 1 ጴጥ. 1፥18-20።
4. ከሁሉም ነገሮች ጋር ሲነጻጸር ክርስቶስን ስለማወቅ የሚሰጡት ግምት——ቁ. 8፤ 2 ጴጥ. 1፥2-3፣ 8፤ 2፥20፤ 3፥18።
5. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ እንደ ተአምራዊ የመዝገብ መዋቀር የመላው መጽሐፍ ቅዱስ መደምደሚያ ለመሆን እንደ ሦስት መሠረታዊ መንስኤዎች ከዋጃቸው ጋር አብሮ የተሠራው እና የተዋቀረው ሦስታንዱ አምላክ፣ መለኮታዊው ሥላሴ እንደሆነ ለማየት ራእይ ያስፈልገናል—ወርቁ እንደ የከተማይቱ መሠረት እግዚአብሔር አብን ያመለክታል፤ ዕንቁዎቹ እንደ የከተማይቱ ደጆች እግዚአብሔር ወልድን ያመለክታሉ፤ የከተማይቱ የኢያስጴድ ቅጥር እግዚአብሔር መንፈስን ያመለክታል——ራእ. 21፥18-21፤ ተዛ. 1 ቆሮ. 3፥12።

ለ. ወደር እንደሌለው-የላቀው ድርሻችን ክርስቶስን እና እርሱ የሆነውን ሁሉ ባለማቋረጥ እንድንመርጥ በዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ- ሃሳባችን ጥልቅ-ዝርዝር የሆነ ለውጥ ይኖረን ዘንድ ብርሃን እንዲሰጠን ጌታን መጠየቅ ያስፈልገናል——ማር. 9፥7-8፤ 2 ቆሮ. 2፥10፤ 4፥7፤ 1 ጴጥ. 1፥8።

ሐ. “የከበረውንም ከተዋረደው ብትለይ፣ እንደ አፌ ትሆናለህ”——ኤር. 15፥19፤ ተዛ. ቁ. 16፦

1. የሚመግብ ወተት እና ለጋ ማር እንደሚፈስባት እንደ መልካሚቱ ምድር እውነታ ጌታን በቃሉ በመቅመስ፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሙሉ መዳን እናድለው ዘንድ፣ ድርሻችን ከሆነው [ቁሳዊ] ምግባችን ይልቅ የጌታን ቃሎች ውድ አድርገን መያዝ አለብን—— ኢዮ. 23፥12፤ 1 ጴጥ. 2፥2-5፤ መዝ. 119፥103፤ ዘዳ. 8፥8፤ መኃ. 4፥11።
2. ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ብልጥግናዎች ልዩ ልዩ እንደሆነው የእግዚአብሔር ጸጋ እናድል ዘንድ የእግዚአብሔር ንግግሮችን መናገር እንድንችል የጌታን ቃሎች ከምድራዊ ብልጥግናዎች ሁሉ በላይ ውድ አድርገን መያዝ አለብን— መዝ. 119፥72፣ 9-16፤ ኤፌ. 3፥8፤ 2 ቆሮ. 6፥10፤ 1 ጴጥ. 4፥10-11።

**II. ለአማኞቹ ክርስቶስ ራሱ ውድነት እንደሆነ ጴጥሮስ አየ—2፥7፤ ተዛ. ፊልጵ. 3፥8፦**

ሀ. ጴጥሮስ በጌታ እጅግ ከመማረኩ (ከመሳቡና ትኩረቱ ከመያዙ) የተነሣ፣ ምንም እንኳን በጌታ ብዙ ጊዜ ቢገሥጽ እና ፈጽሞ ቢወድቅም፣ እስከ ሰማእትነቱ ድረስ ጌታን እንደ እረኛው ተከተለው——ሉቃ. 5፥8-11፤ ማር. 14፥67-72፤ 16፥7፤ ዮሐ. 21፥15-22፤ 2 ጴጥ. 1፥14-15፡-

1. ለመጀመሪያ ጊዜ የጌታን ግርማ የተመለከቱት ይሆኑ ዘንድ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ ጌታ በክብር በተለወጠበት እጅግ ከፍተኛ ጅማሬ ተቀባይነትን እንዳገኙ ጴጥሮስ ተገነዘበ——ቁ. 16-18፤ ተዛ. 1 ጴጥ. 5፥1።
2. በዕርገቱ፣ ክርስቶስ “ግርማዊ” ነው—ለሙሉ መዳናችን ድሰታችን ይሆን ዘንድ ራሱን ወደ ውስጣችን ለማደል (ራእ. 22፥1) እንደ ዳኛ፣ እንደ ሕግ ሰጪው እና በእግዚአብሔር አገዛዝ ውስጥ እንዳለው ንጉሣችን (ኢሳ. 33፥21-22)፣ እርሱ አምላካችን እና አዳኛችን (2 ጴጥ. 1፥1) እና የሁሉ ጌታ (1 ጴጥ. 3፥22፤ ሐዋ. 2፥36) ነው።

ለ. ለእግዚአብሔር ግንባታ ክቡሩ ድንጋይ ክርስቶስ ራሱ ነው—1 ጴጥ. 2፥4፣ 6-8።

ሐ. ክቡሩ የክርስቶስ ደም ከከንቱ ኑሯችን ዋጅቶናል—1፥14፣ 18-19።

መ. ክቡር እና እጅግ ታላቅ የሆኑት የተስፋ ቃሎች አምላካችን እና አዳኛችን በሆነው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ተሰጥተውናል— 2 ጴጥ. 1፥1፣ 4፤ ተዛ. ኢሳ. 42፥6፤ ዕብ. 8፥8-12፡-

1. የጌታን ውድ ስም በመጥራት፣ ለእግዚአብሔር ግንባታ ግብ ክቡር እና እጅግ ታላቅ እንደሆኑት የእግዚአብሔር ተስፋ ቃሎች ጌታን በመደሰት፣ የመዳን ጽዋ ከእርሱ እንጠጣለን——ሐዋ. 4፥10-12፤ መዝ. 116፥12-13።
2. እነዚህ ክቡር የተስፋ ቃሎች አካል የለበሱት በእግዚአብሔር ቃል ነው፤ የተስፋ ቃሎቹን እየጸለዩ-በማንበብ፣ ወደ ጌታችን እና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥት በሙላት መግባትን እንደሰት ዘንድ እስከ ሕይወት ብስለት በሕይወት እንድናድግ እና እንድንዳብር መለኮታዊውን ባሕርይ እንካፈላለን፣ እንደሰትማለን——2 ጴጥ. 1፥ 4-11።

ሠ. እግዚአብሔር ለአማኞች ሁሉ እኩል የከበረ እምነትን ሰጥቷል——ቁ. 1፤ ሮሜ 12፥3።

ረ. የእምነታችን የከበረ መፈተን የሚከናወነው፣ በምናልፍባቸው መከራዎች በኩል በሚመጡት በተለያዩ ፈተናዎች አማካኝነት ነው——1 ጴጥ. 1፥6-7።

**III. ኢሳይያስ ክርስቶስን በክብር ውስጥ ያየበትብን ራእይ ያየው ተስፋ በቆረጠበት ሁኔታ ውስጥ ነበር——ኢሳ. 6፥1-8፤ ተዛ. 5፥ 20፤ 22፥1፤ 2 ዜና 26፥1-5፡-**

ሀ. በኢሳይያስ ዘመን የነበረው ክፉ ጊዜ በጌታ የማስጠንቀቂያ ቃል ይታያል—“ክፉውን መልካም/ መልካሙን ክፉ ለሚሉ፥
/ ጨለማውን ብርሃን/ ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፥/ ጣፋጩን መራራ/ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ/ ወዮላቸው!”——ኢሳ. 5፥20።

ለ. የእግዚአብሔር የተመረጠ እና የተወደደ ሕዝብ ዓመፅ፣ በደሎች እና መበላሸቶች ቢኖርበትም፣ ክርስቶስ እንደ ጌታ፣ እንደ ንጉሥ፣ እንደ የሠራዊት ጌታ አሁንም በክብር በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጧል—6፥1-5፤ ሰቆ. 5፥19፤ ራእ. 22፥ 1።

ሐ. በኢሳይያስ የታየው ማንነት ክርስቶስ ነበር—ኢሳ. 6፥5፤ ዮሐ. 12፥38-41፦

1. ዮሐንስ፣ በምድር ላይ የነበረውን የክርስቶስን ኑሮ እና ሥራ ሲዘግብ፣ ኢሳይያስ "ክብሩን...አየ...ስለ እርሱም ተናገረ" አለ—ቁ. 41።

2. የከበረውን በዙፋኑ ላይ ያለውን የክርስቶስን ራእይ ለማየት፣ የዓይነ ስውርነታችንን እና የበሽታችንን የውስጥ ፈውስ እንቀበል ዘንድ፣ ጌታ የውስጥ ዓይኖቻችንን እንዲከፍት፣ ልባችንን እንዲያለሰልስ እና ልባችን ወደ እርሱ ዞሮ እንዲቆይ ለመጸለይ መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ኢሳይያስ ለሰጠው የማስጠንቀቂያ ቃል (ኢሳ. 6፥9-11) ግድ መሰኘት አለብን (ዮሐ. 12፥40፤ ማቴ. 13፥14-17፤ ሐዋ. 28፥25-27፤ ራእ. 3፥18፤ 4፥2፤ 2 ቆሮ. 3፥16-18)።

መ. የክርስቶስ ረጅም የልብሱ ዘርፍ፣ በስብዕናው ውስጥ እና በስብዕናው በኩል በዋናነት የተገለጠውን በሰናይ ባሕርያቱ ውስጥ ያለውን ውበት ያመለክታል፤ ክርስቶስ ረጅም ዘርፍ ያለው ልብስ መልበሱ ለኢሳይያስ በሰው መልክ እንደተገለጠለት ያመለክታል፤ ክርስቶስ በስብዕና ሰናይ ባሕርያቱ በሚገለጠው መለኮታዊው ክብር በዙፋን ላይ የተቀመጠው አምላክ-ሰው ነው—ኢሳ. 6፥1፤ ተዛ. ሕዝ. 1፥26፣ 22፤ ሐዋ. 2፥36፤ ዕብ. 2፥9።

ሠ. ክርስቶስን የጽድቁ መሠረት በሆነው በቅድስናው ኢሳይያስ አየው—ኢሳ. 6፥2-3፦

1. ሱራፌል የሚያመለክቱት ወይም የሚወክሉት የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የሆነውን የክርስቶስን ቅድስና ነው፤ በዚያ የቆሙት ለክርስቶስ ቅድስና ነበር።

2. የክርስቶስ ቅድስና በጽድቁ ላይ የተመሠረተ ነው፣ ክርስቶስ ሁሌም ጻድቅ ስለነበር፣ ከተራ ሰዎች ተለይቷል፣ ተቀድሷል—5፥16።

ረ. ይህን ራእይ ከማየቱ የተነሣ ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው ሰዎች መካከል የሚኖር፣ ከንፈሮቹ የረከሱበት ሰው እንደነበር በመገንዘብ ኢሳይያስ ተወገደ፣ አበቃለት—6፥5፦

1. በአዲስ ኪዳን ግንዛቤ፣ እግዚአብሔርን ማየት እግዚአብሔርን ከማትረፍ ጋር እኩል ነው፤ እግዚአብሔርን ማትረፍ ማለት በእግዚአብሔር እንቀናበር ዘንድ እግዚአብሔርን በንጥረ ነገሩ፣ በሕይወቱ እና በባሕርይው መቀበል ነው— ተዛ. ዘፍ. 13፥14-15፤ ገላ. 3፥14፤ ማቴ. 5፥8።

2. እግዚአብሔርን ማየት ይለውጠናል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔርን በማየት ውስጥ እግዚአብሔርን እናተርፋለን፣ ንጥረ ነገሩን ወደ ውስጣችን እንቀበላለን፣ አሮጌው ንጥረ ነገራችን ይወገዳል፤ ይህ ገንባፍራሽ ሂደት ልውጠት ነው—2 ቆሮ. 3፥16—4፥1፤ ሮሜ 12፥2፤ ፊልጵ. 3፥8።

3. እግዚአብሔርን ይበልጥ ባየን፣ ባወቅን፣ እና በወደድን መጠን፣ ራሳችንን ይበልጥ እንጸየፋለን፣ ራሳችንን ይበልጥ እንክዳለን—ኢዮ. 42፥5-6፤ ማቴ. 16፥24፤ ሉቃ. 9፥23፤ 14፥26።

ሰ. ኢሳይያስ የረከሰ እንደነበር ከተገነዘበ በኋላ፣ ከመሠዊያው በተወሰደ ፍም የእግዚአብሔርን ቅድስና ከሚያመለክቱት ከሱራፌል በአንዳቸው ነጻ፦

1. ይህ ፍም ከሱራፌል በአንዳቸው መተግበሩ የሚያመለክተው በመስቀል ላይ የተፈጸመውን እና በሚፈርደው፣ በሚያቃጥለው እና በሚቀድሰው ኃይሉ "በቅዱሱ መንፈስ" የተተገበረውን የክርስቶስን ቤዛነት ፍቱንነት ነው—ኢሳ. 6፥6-7፤ 4፥4፤ ተዛ. ሉቃ. 12፥49፤ ራእ. 4፥5።

2. እግዚአብሔርን ማየት በእግዚአብሔር መጥራትን፣ መንጻትን ያመጣል፤ በእግዚአብሔር መንጻት ደግሞ፣ በክብሩ እንዲገለጠው፣ በቅድስናው ፈጽሞ እንዲሰረጽ እና በጽድቁ እንዲኖር፣ የተመረጠው ሕዝቡ ክርስቶስን ወደሚኖርበት ሁኔታ ለማምጣት በእግዚአብሔር መላከን ያመጣል—ኢሳ. 6፥6-8፤ 1 ዮሐ. 1፥7-9፤ ሐዋ. 13፥47፤ ፊልጵ. 1፥21።

**IV. በላቀው ውድነቱ እንደ ሰው ለዳንኤል የተገለጠው የላቀው ክርስቶስ ራእይ፣ ዳንኤል አድናቆትን፣ መጽናናትን፣ መበረታታትን እና መረጋጋትን ያገኘ ዘንድ ነበር—ዳን. 10፥4-9፦**

ሀ. ክርስቶስ የተመረጠውን ሕዝቡን በምርኳቸው ለመንከባከብ፣ በበፍታ በተመሰለው ልብስ በስብዕናው እንደ ካህን ተገለጠ—ቁ. 5፤ ዘጸ. 28፥31-35።

ለ. ክርስቶስ በአሕዛብ ሁሉ ላይ ለመግዛት፣ በወርቅ የወገብ መታጠቂያ በተመለከተው በመለኮትነቱ በንግሥናው ተገለጠ— ዳን. 10፥5።

ሐ. ክርስቶስ የእርሱ ሕዝብ ያደንቀው ዘንድ፣ እንደ ቢረሌ በሚመስል አካሉ በተመለከተው፣ በውድነቱ እና በክብረቱ ተገለጠ፤ ክርስቶስ አካል በመልበሱ መለኮት (ቢጫ)፣ በሕይወት የተሞላ (አረንጓዴ) እና ሰማያዊ (ሰማያዊ ቀለም) መሆኑን በማመልከት በዕብራይስጥ ቢረሌ የሚለው ቃል፣ ሰማያዊያማ-አረንጓዴ ወይም ቢጫ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይን ሊያመለክት ይችላል—ቁ. 6።

መ. ክርስቶስ እንደ መብረቅ ምስያ በሚመስል ፊቱ እንደተመለከተው (ቁ. 6) በሕዝቡ ላይ ለማብራት በብሩህነቱ፣ የሚንበለበል ፋና በሚመስሉ ዓይኖቹ በተመለከቱት (ቁ. 6) ሰዎችን ለመመርመር እና ለመፍረድ አብርሆት በሚሰጥ እይታው ተገለጠ።

ሠ. ክርስቶስ የሚያንጸባርቅ የጋለ ናስ በሚመስሉ ክንዶቹና እግሮቹ እንደተመለከተው (ቁ. 6)፣ በሥራው እና በእንቅስቃሴው ማንጸባረቅ ለዳንኤል ተገለጠለት—ቁ. 6።

ረ. ክርስቶስ ሰዎች ላይ ለመፍረድ፣ የብዙ ሕዝብ ድምፅ በሚመስል ድምፁ እንደተመለከተው (ቁ. 6) በጠንካራ ንግግሩ ተገለጠ፦

1. ለክርስቶስ በሁሉ ነገር ፊተኛውን ስፍራ ለመስጠት፣ ክርስቶስ በሁሉ ነገር ፊተኛ ስፍራ እንዲኖረው ለማድረግ መላው የዓለም ሁኔታ በሰማያት አምላክ የሰማይ አገዛዝ ሥር ነው—2፥34-35፤ 7፥9-10፤ 4፥34-35፤ ቆላ. 1፥15፣ 18፤ ራእ. 2፥4-5።

2. በግል አጽናፍ ዓለማችን ውስጥ ክርስቶስ የመጀመሪያው ስፍራ፣ ፊተኛው ስፍራ ሊኖረው ይገባል፤ ዛሬ ክርስቶስ፣ ፊተኛው ስፍራ ያለው እርሱ፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን፣ በቤተሰብ ሕይወታችን እና በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ማዕከል እና አጽናፍ ዓለም ሊሆን ይገባል—ቆላ. 1፥17፣ 18፤ 3፥17፤ 1 ቆሮ. 10፥31።

3. ክርስቶስን ለእኛ ማዕከል (አንደኛ) እና አጽናፍ ዓለም (ሁሉ ነገር) ለማድረግ በሰማያዊ አገዛዙ ሥር እግዚአብሔር ከባቢ ሁኔታን እየተጠቀመ ነው—ሮሜ 8፥28፤ ቆላ. 1፥18፥ 27፤ 3፥4፣ 10-11።

4. ክርስቶስ ፊተኛው ስፍራ እንዲኖረው ሕዝቡ ለመሆን በእግዚአብሔር እንደተመረጠ ሕዝብ ክርስቶስን ፊተኛ ለማድረግ፣ በሁሉም ነገር የመጀመሪያ ስፍራ እንዲኖረው ለማድረግ በእግዚአብሔር ሰማያዊ አገዛዝ ሥር ነን—ዳን. 4፥26፣ 35፤ ቆላ. 1፥18፤ 3፥4፣ 10-11፤ መዝ. 27፥4።

**V. እንደ የግል መዝገቡ የውድነት ሰዎች ሆነን በክርስቶስ መቀናበር እንችል ዘንድ፣ ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔር የላቀ ውድነት ለመደሰት ጊዜውን መዋጀት አለብን፤ እኛን እንደ መዝገቡ እንደሚደሰትተን ሁሉ እርሱን እንደ እድል ፈንታችን በመደሰት ውድ በሆነው መገኘቱ ስንኖር፣ ለልቡ መሻት መፈጸም የእርሱ መንፈሳዊ ቤት፣ የእርሱ ቅዱስ እና ንጉሣዊ የካህናት ቡድን ያደርገን ዘንድ ራሱን ወደ ውስጣችን ይገነባል—1 ጴጥ. 3፥4፤ ዳን. 9፥23፤ 10፥11፣ 19፤ 2 ቆሮ. 2፥10፤ መዝ. 16፥5፤ ዘጸ. 19፥4-6፤ 1 ጴጥ. 2፥1-9፤ 2 ጴጥ. 3፥8፣ 11-12።**

## መልእክት ሦስት የቡድን የንባብ ክፍል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ጴጥ. 1፥7፣ 19፤ 2፥4፣ 6-7፤ 3፥4፤ 2 ጴጥ. 1፥1፣ 4

ሰው ብዙውን ጊዜ የአንድን ነገር ዋጋ የሚለካው ስለ ነገሩ ባለው እውቀት መሠረት ነው። በማቴዎስ 23፥16-26፣ ዓይኖቻቸው በቤተ መቅደሱ ውበት ላይና አብዛኛው ክፍሉ ከወርቅ መገንባቱ ላይ የሆኑ ሰዎችን እናገኛለን። ቤተ መቅደሱን እጅግ ዋጋ ያለው ነገር አድርገው ይቆጥሩት ነበር። አንዳንዶች መሠዊያውን ያዩና በላዩ ላይ ከሚሠዉት በሬዎች፣ በጎች እና ርግቦች ጋር ያነጻጽሩታል። መሠዊያው ትንሽ ዋጋ እንዳለው፣ በሬዎቹ፣ በጎቹ እና ርግቦቹ ግን ብዙ ዋጋ እንዳላቸው ቆጠሩ። አንዳንዶች ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን አሥራት ያወጣሉ፤ በሕግ ያሉትን ዋና ነገሮች—ፍትሕን፣ ምሕረትን እና ታማኝነትን ግን ችላ ብለዋል። አንዳንዶች ስለ ሁሉም ነገር እጅግ ጠንቃቃ ነበሩ። ትንኝን ያጠራሉ፤ ግመልን ግን ይውጣሉ። አንዳንዶች ጽዋውን እና ወጭቱን ለመጠቀም በችኮላ ላይ ናቸው። ውጫቸውን ያነጻሉ፣ ውስጣቸው ግን በርኩሰት የተሞላ ነበር...በማቴዎስ 23፥16-26፣ ጌታ ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች ደንቆሮዎች፣ ዕውሮች እና ግብዞች ብሎ ጠርቷቸዋል፤ ምክንያቱም እውነተኛውን የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳብ አያውቁም ነበር። የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳባቸው ሙሉ በሙሉ የተሳሳተ ነበር።

አንዴ ሰው ከዳነ በኋላ የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳቡ ይለወጣል። በአንድ ወቅት ይወደው የነበረውን አሁን አይወደውም፤ በአንድ ወቅት ይንቀው የነበረውን ደግሞ አሁን እንደ ውድ ይቆጥረዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳባችንን መለወጥ በተመለከተ ብዙ የሚናገረው አለ። በዚህ ለውጥ ላይ ያተኮሩ ምንባቦች ለአዲስ አማኞች ብርሃን ሊሰጡ ይችላሉ። እነዚህ ምንባቦች አንድ ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባውን ተገቢ የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳብ ያሳዩናል።

መዝሙር 118፥22...የዋጋ አሰጣጥ ለውጥን ያመለክታል። ግንበኞች በዓይናቸው ጥቅም እንደሌለው የቆጠሩትን ድንጋይ ናቁት። በአይሁድ መሪዎች ዓይን ክርስቶስ የማያስፈልግ ነበር፤ ስለዚህም ሊያስወግዱት ፈለጉ። ነገር ግን ይህ የተናቀ ድንጋይ፣ አዲስ ለተመሠረተው መዳን የማዕዘን ድንጋይ ለመሆን ተመርጧል። በአይሁድ ግንበኞች የተናቀውን የማዕዘን ድንጋይ እግዚአብሔር አከበረው፤ ለማዳኑ ግንባታም ተጠቀመው። እነዚህ ሁለት ዓይነት የዋጋ አሰጣጦች ምንኛ የተለያዩ ናቸው! አዲስ አማኞችን በዋጋ አሰጣጣጣቸው እንዲህ ወዳለው ለውጥ እንዲመጡ ማድረግ አለብን። በፊት ስለ ክርስቶስ ምን ዓይነት እይታ እንደነበራቸው እና አሁን ደግሞ ምን ዓይነት እይታ እንዳላቸው መጠየቅ ይኖርብናል። በአንድ ወቅት ዋጋ ያልነበረው ነገር አሁን በዋጋ ሊተመን የማይችል እንደሆነ ልናሳያቸው ይገባል...ሌሎች ክርስቶስን ንቀውታል፤ እኛ ግን እናከብረዋለን።

አንደኛ ቆሮንቶስ 1፥18 እንዲህ ይላል፡- "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና"...አንድ ሰው ከመዳኑ በፊት መስቀሉን ዋጋ እንደሌለው ነገር ይቆጥረዋል። ከዳነ በኋላ ግን፣ እንደ የእግዚአብሔር ኃይል፣ የከበረ እና ውድ እንደሆነ ነገር ያየዋል። ሰው አንዴ በጌታ ካመነ በኋላ፣ የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳቡ ወዲያውኑ ይለወጣል። የመስቀሉ ማዳን እጅግ ውድ የሆነ ነገር ይሆናል።

ማቴዎስ 10፥37-38...አባት፣ እናት፣ ሚስት እና ልጆች ለሰው እጅግ ውድ የሆኑ ነገሮች እንደሆኑ ያመለክታል። እነዚህ ነገሮች፣ ሰው በዚህ ሕይወት ያለው እጅግ ዋጋ ያላቸው ነገሮች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ከጌታ ጋር ካልተነጻጸሩ፣ እነርሱን መውደድ ምንም ስሕተት የለውም። ይሁን እንጂ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ያለብን ሁኔታ ሲፈጠር፣ የትኛውን እንመርጣለን?... ዘመዶቻችን ውድ ናቸው፤ ከጌታ ጋር ግን የሚወዳደሩ አይደሉም። ጌታችን ከዘመዶቻችን ሁሉ የበለጠ ውድ ነው።

ኢዮብ 22፥23-28 እንዲህ ይላል፡- "ሁሉን ወደሚችል አምላክ ብትመለስ፥ ትጠገናለህ፥ ኃጢአትንም ከድንኳንህ ብታርቅ፥ የወርቅን ዕቃ በአፈር ውስጥ፥ የኦፊርንም ወርቅ በጅረት ድንጋይ መካከል ብትጥል፥ ሁሉን የሚችል አምላክ ወርቅና የሚብለጨለጭ ብር ይሆንልሃል። የዚያን ጊዜ ሁሉን በሚችል አምላክ ደስ ይልሃል፥ ፊትህንም ወደ እግዚአብሔር ታነሣለህ። ወደ እርሱም ትጸልያለህ፥ እርሱም ይሰማሃል፤ ስእለትህንም ትሰጣለህ። ነገርንም ትመክራለህ፥ እርሱም ይሳካልሃል፤ ብርሃንም በመንገድህ ላይ ይበራል።" ከቁጥር 24 ጀምሮ ያሉት ነገሮች ሁሉ በቁጥር 23 ላይ የተመሠረቱ ናቸው...ሰው ከኃጢአት (ጽድቅ ካልሆነው) ለመራቅ እና ራሱን ሁሉን በሚችል አምላክ ለማስደሰት ሲል፣ የወርቅን ዕቃ፣ የኦፊርንም ወርቅ እና ውድ የሆነን ብር በአፈር ውስጥ እና በጅረት ድንጋይ መካከል ይጥላል። እዚህ ጋር እንደገና የዋጋ አሰጣጥ ለውጥን እናያለን። እንዲህ ባለ ወሳኝ ነጥብ ላይ ብንፈተን እና ከወርቅ ዕቃ፣ ከኦፊር ወርቅ፣ ከውድ ብር እና ከያህዌ አንዳቸውን እንድንመርጥ ብንጠየቅ የትኛውን እንመርጣለን? እንዲህ ያለው ምርጫ የእግዚአብሔር የሆኑትን የእርሱ ካልሆኑት ይለያል። የእግዚአብሔር የሆኑት ሁሉ በእርግጥ ያህዌን እንደ ደስታቸው ይመርጡታል። ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር ማንሣት ይችላሉ፤ በሦስት ነገሮችም በእግዚአብሔርም ይባረካሉ። በመጀመሪያ፣ ጸሎታቸው ይሰማል። የወርቅን ዕቃ፣ የኦፊርን ወርቅ እና የሚብለጨለጭን ብር የሚመርጡት ጸሎታቸው አይሰማም። ሁለተኛ፣ ጌታ ያህዌ በምርጫቸው እና በውሳኔያቸው ደስ ይለዋልና፣ ምክራቸውንም ሁሉ ያሳካላቸዋል። ሦስተኛ፣ ብርሃን በመንገዳቸው ላይ ይበራል። የመንገዳቸው እያንዳንዱ እርምጃ በብርሃን የተሞላ ይሆናል። ይህ ወደ እግዚአብሔር የዞሩ ሰዎች የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳብ ለውጥ ውጤት ነው። ይፍጠንም ይዘግይም አንድን አዲስ አማኝ ከአሮጌው ክልሉ እንዲወጣ መርዳት አለብን፤ ከራሱ ፅንሰ-ሃሳቦች ልናድነው ይገባል። አንድ ሁኔታ ሲፈጠር፣ "የትኛውን ትመርጣለህ?" ብለን ልንጠይቀው ይገባል። የእግዚአብሔርን ጽድቅ እንዲመርጥ፣ የወርቅን ዕቃ፣ የኦፊርን ወርቅ እና የሚብለጨለጨውን ብር ደግሞ እንዲጥል ልንረዳው ይገባል። የጽድቅ ዋጋ ከየትኛውም ውድ መዝገብ በላይ ነው።

ፊልጵስዩስ 3፥7-8፣ "ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ። አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ" ይላል። እዚህ ጋር ጳውሎስ እንዲሁ የዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳብ ለውጥ እንደነበረው ማየት እንችላለን። ለእርሱ ረብ የነበራቸውን ነገሮች፣ ስለ ክርስቶስ እና ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጠው ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ እውቀት እንደ ጉዳት ቆጥሯቸዋል።

ኤርምያስ 15፥19፣ የከበረውን ከተዋረደው ብንለይ እንደ እግዚአብሔር አፍ እንደምንሆን ይነግረናል። የነገሮችን ተገቢ ዋጋ መናገር የማንችል ከሆነ፣ እግዚአብሔር አይቀበለንም፤ ገሸሽም ያደርገናል...በዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳብ እንዲህ ያለን ለውጥ የማምጣትን አስፈላጊነት ልናይ ይገባል። እጅግ የላቀውን ክፍል መምረጥን ማወቅ እንችል ዘንድ በዋጋ አሰጣጥ ፅንሰ-ሃሳባችን ጥልቅ ዝርዝር የሆነ ለውጥ እንዲኖረን ጌታ ብርሃንን ይስጠን። (CWWN, vol. 60, pp. 387-395)

የእግዚአብሔር የተመረጡ እና የተወደዱ ሕዝብ የሆኑት እስራኤል ዓመፅ፣ በደሎች እና ዝቅጠቶች ቢኖርባቸውም፣ ክርስቶስ አሁንም በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ በክብር ተቀምጧል (ኢሳ. 6፥1-4)። በምድር ላይ ሁኔታው ምንም ቢሆን፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለው ጥፋትና ዝቅጠት ምንም ቢሆን፣ ክርስቶስ አሁንም በዙፋኑ ላይ በክብሩ እንዳለ እነዚህ ጥቅሶች ያመለክታሉ።

ኢሳይያስ በእስራኤል ልጆች መካከል ያለውን ሁኔታ ሲመለከት እጅግ አዘነ...የክብርን ጌታ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ያየው ዘንድ፣ ጌታ ወደ ራእይ ውስጥ ያስገባው በዚህ ጊዜ ነበር (ቁ. 1)። ጌታ ኢሳይያስን እንዲህ እያለው ይመስላል፡- "ወደ ታች ሁኔታውን አትመልከት። ወደ ታች ካየህ ታዝናለህ። ወደ ላይ እኔን ተመልከት። አሁንም እዚህ ነኝ። በዚያ ምንም መልካም ነገር ላይኖር ይችላል፤ በዚህ ግን ሁሉ መልካም ነው። በአጽናፍ ዓለም ውስጥ ያለ ብቸኛው መልካም ነገር እኔ ነኝ። እኔን ተመልከት።"

ሰዎቹ ወድቀዋል፤ ክርስቶስና ዙፋኑ ግን በክብሩ ያው ናቸው (ቁ. 1)። በዚህ ምድር ላይ እያንዳንዱ ነገር ይቀያየራል፤ ይለዋወጥማል፤ ክርስቶስ ግን ዛሬም ለዘላለም ያው ሆኖ ይኖራል (ዕብ. 13፥8)።

የክርስቶስ የልብሱ ዘርፍ አሁንም መቅደሱን ሞልቶታል (ኢሳ. 6፥1)። የክርስቶስ ረጅም ልብስ፣ በሰናይ ባሕርያቱ ያለውን የክርስቶስን ግርማ ያመለክታል...በሰናይ ባሕርያቱ ያለው የክርስቶስ ግርማ በዋናነት የተገለጠው፣ በስብዕናው ውስጥ እና በስብዕናው በኩል ነው።

ኢሳይያስ በክብር ላለው የክርስቶስ ራእይ "ጠፍቻለውና ወዮልኝ!" (ቁ. 5) በማለት ምላሽ ሰጥቷል። ይህን ራእይ ከማየቱ የተነሣ፣ ኢሳይያስ ተወገደ፤ አበቃለት።

ለከንፈሮቻችን፣ ለንግግራችን ትኩረት መስጠት አለብን (ተዛ. ቁ. 5)። በየቀኑ ብዙ እናወራለን። የምንናገራቸው አብዛኞዎቹ ቃላት ከፉ ናቸው፤ ምክንያቱም የምንናገራቸው አብዛኞዎቹ ቃላት የትችት ቃላት ናቸው። ስለ ማንኛውም ጉዳይ ወይም ስለ ማንኛውም ሰው የምንናገረው እያንዳንዱ ቃል የትችት ቃል ነው ማለት ይቻላል። ከንፈሮቻችን የረከሱ የሆኑት በዚህ ምክንያት ነው...ሐሜትን፣ ማጉረምረምንና ክርክርን ካስወገድን፣ የምናወራው እጅግ ጥቂት ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። እንደ ኢሳይያስ ከንፈሮቻችን የረከሱ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልገናል።

የጌታን ራእይ በእውነት ያየ ሁሉ፣ አብርሆትን ያገኛል። ያየው ራእይ ወዲያውኑ ያጋልጠዋል፤ ወደ ብርሃንም ያመጣዋል። በሉቃስ 5 ጴጥሮስ ጌታን ባየው ጊዜ፣ ወዲያውኑ ጌታን፣ "ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝና ከእኔ ተለይ" ብሎታል (ቁ. 8)።

በልምምዳችን ንጹሕ መሆናችን ወይም አለመሆናችን የሚመረኮዘው በሕሊናችን ስሜት ላይ ነው፤ የሕሊናችን ስሜት ደግሞ ጌታን በማየታችን ላይ ይመረኮዛል። ጌታን የምናይበት መጠን፣ የምንነጻበትን መጠን ይወስናል። ጌታን ይበልጥ ባየነውና በተጋለጥን መጠን፣ ይበልጥ እንነጻለን። ሕሊናችን ሲነጻ እና በደል የሌለበት ሲሆን፣ እግዚአብሔርን መንካት እንችላለን። አብርሆት ካገኘው ሕሊናችን አንጻር ንጹሕ ነን፤ በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታችን አንጻር ግን ንጹሕ አይደለንም...በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ እስካለን ድረስ፣ መቼም ሙሉ በሙሉ ልንነጻ አንችልም፤ ምክንያቱም አሮጌው ፍጥረት ንጹሕ አይደለም። የሰውነታችን ቤዛነት ያስፈልገናል። ሰውነታችን ቤዛነቱን ካገኘ በኋላ፣ ከአሮጌው ፍጥረት እንወጣለን። በዚያን ጊዜ፣ ሙሉ በሙሉ ንጹሕ እንሆናለን። (Life-study of Isaiah, pp. 35-39)

እግዚአብሔርን ማየት እግዚአብሔርን ከማትረፍ ጋር እኩል ነው። እግዚአብሔርን ማትረፍ፣ እግዚአብሔርን በንጥረ ነገሩ፣ በሕይወቱ እና በባሕርይው መቀበል ነው። በመጨረሻ፣ ይህ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ማድረግ ብቻ ሳይሆን...በእርሱ እንድንቀናበርም ያደርገናል፤ ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ተመላኪነት ምንም ድርሻ የለንም።

በእግዚአብሔር የተዋጁ፣ ዳግም የተወለዱ፣ የተቀደሱ፣ የተለወጡ፣ የልጁን መልክ የመሰሉና የከበሩ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፊት ያያሉ (ራእ. 22፥4)። እግዚአብሔርን ማየት ይለውጠናል (2 ቆሮ. 3:18)፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን በማየት የእርሱን ንጥረ ነገር ወደ ውስጣችን እንቀበላለን። እግዚአብሔርን ስንቀበል፣ አዲስ ንጥረ ነገር ወደ እኛ ይመጣል፤ አሮጌው ንጥረ ነገርም ይወገዳል። ይህ ገንባ-አፍራሽ ሂደት ለውጥ (metabolic transformation) ነው። እግዚአብሔርን ማየት ወደ ክቡሩ የእግዚአብሔር መልክ መለወጥ ነው። ይህም እግዚአብሔርን በሕይወቱ መግለጥ እና በሥልጣኑ መወከል እንችል ዘንድ የእግዚአብሔር ክፍል ያደርገናል።

ኢዮብ እግዚአብሔርን እንዳየ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱንም እንደ ናቀ ተናግሯል። በልምምዳችን መሠረት፣ እግዚአብሔርን ይበልጥ ባየነውና በወደድነው መጠን፣ ራሳችንን ይበልጥ እንንቃለን። እግዚአብሔርን ይበልጥ ስናውቀው፣ ራሳችንን ይበልጥ እንክዳለን። (Life-study of Job, pp. 157-158)

## መልእክት አራት

### ክርስቶስ እንደ ሰናይ ባሕርያታችን፣ እንደ የእግዚአብሔር ሰላም፣ እንደ ምሥጢራችን እና ኃይል እንደሚሰጠን ማንነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ፊልጵ. 4፥5-9፤ 11-13

I. **ለልምምዳችን በፊልጵስዩስ 4፥5-9 ያሉት የክርስቶስ ሰናይ ባሕርያት ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት መገለጫ ናቸው—1፥19- 21፤ 2፥5-13፤ 3፥8-10፦**

ሀ. ጳውሎስ ገርነትን እና የጭንቀት አለመኖርን ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ገጽታዎች አድርጎ ይቆጥራቸዋል።

ለ. ከሰይጣን የሚመጣው ጭንቀት፣ የስብዕና ሕይወት ጥቅል ድምር ነው፣ የአማኞችንም ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ይረብሻል፤ ከእግዚአብሔር የሚመጣው ገርነት፣ ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ጥቅል ድምር ነው፤ ሁለቱ ተቃራኒ ናቸው—ማቴ. 6-22-34።

II. **"ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ። ጌታ ቅርብ ነው"—ፊልጵ. 4፥5፦**

ሀ. ሁሉንም የክርስትና ሰናይ ባሕርያት ስለሚያካትት በክርስቲያን ልምምድ መሠረት ገርነት ሁሉን-ያካተተ ነው፤ በእርግጥ ገርነት ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ ሁሉን እንዳካተተው መንፈስ ከተትረፈረፈው አቅርቦቱ ጋር ነው—1፥19-21፦

1. ገርነት የራስን ሕጋዊ መብት በመጠየቅ ባለመናጠቅ ፍትሐዊነት፣ አሳቢነት እና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት አስተዋይነት ነው፤ ገርነት ማለት የሚገባንን ባናገኝም በቀላሉ እንረካለን ማለት ነው፦

   ሀ. ገርነት ፍቅርን፣ ትዕግሥትን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ ርኅራኄን፣ አሳቢነትን እና መገዛትን፣ ለመረታት ፈቃደኛ መሆንን ያካትታል፤ እንዲህ ያለ ሁሉን-ያካተተ ሰናይ ባሕርይ ካለን፣ ጽድቅ እና ቅድስናም ይኖረናል።

   ለ. ገርነት ራስን መግዛትን፣ መመጠንን፣ ጨዋነትን፣ መረዳትን፣ ሃዘኔታን፣ ጥበብን፣ ምሕረትን፣ ሰላማዊነትን፣ ወደ ጌታ ማየትን እና ጌታ በሁሉም ነገር ሉዓላዊ መሆኑን ማመንን ጭምር ያካትታል—ተዛ. 2 ቆሮ. 12፥7-9።

2. ገር ሰው ሁልጊዜም የሚገጥም እና ባሕርይው ሁልጊዜ የሚስማማ ነው—ተዛ. 6፥1፤ 10፥1፤ ፊልጵ. 1፥19፤ ኢሳ. 11፥2፦

   ሀ. ገር ከሆንን፣ ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ለማቅረብ ጥበቡ እና ችሎታው ይኖረናል፤ ለእነርሱ ምን እንደምንናገር እና መቼ እንደምንናገር ሙሉ እውቀቱ ይኖረናል—50፥4-5፤ ቆላ. 1፥28፤ ምሳ. 25፥15።

   ለ. ገር መሆን ማለት የምናደርገው ወይም የምንናገረው ነገር ሌሎች ላይ ምን ዓይነት እንድምታ እንደሚያመጣ ማሰብ ነው—2 ዜና 1፥10።

ለ. ሁሉን-እንዳካተተ ሰናይ ባሕርይ፣ ገርነት ክርስቶስ ራሱ ነው፤ ክርስቶስ ገርነት ስለሆነ፣ ለጳውሎስ መኖር ገርነት ነበር— ፊልጵ. 1፥21፦

1. ገርነታችን ለሰዎች ሁሉ እንዲታወቅ መፍቀድ ማለት የምንኖረው እና የምናጎላው፣ እንደ ምሳሌያችን የምንወስደው እና እንደ ግባችን የምንከታተለው ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ እንዲታወቅ መፍቀድ ማለት ነው።
2. ጌታ ኢየሱስ ብቻ በገርነት የተሞላ ሕይወትን ኖሯል፣ ዛሬም ክርስቶስ ብቻ ፍጹም ገርነታችን መሆን ይችላል—ሉቃ. 24፥15-19፣ 28-31፤ ማቴ. 17፥24-27፤ የሐ. 11፥20-34።
3. ገርነታችንን ማሳወቃችን እንደ ስብዕና ሰናይ ባሕርያት ጥቅል ድምር ክርስቶስን የሚገልጥ ሕይወትን መኖር ነው።
4. ጳውሎስ ስለ ገርነት ከተናገረ በኋላ ወዲያውኑ ጌታ ቅርብ ነው ይላል (ፊልጵ. 4፥5)፤ ከስፍራ አኳያ፣ ጌታ በቅርባችን ነው፣ ሊረዳን ዝግጁ ነው፤ ከጊዜ አኳያ፣ ጌታ መምጫው ደርሷል፣ በቅርብ ይመጣል (ተዛ. ሮሜ 10፥8-13)፤ የጌታ ቅርብ መሆን በዋናነት የሚያመለክተው ከእኛ ጋር ያለውን መገኘቱን ነው (ማቴ. 1፥23፤ ዘጸ. 33፥14)።

ሐ. ክርስቶስን እንደ መለወጥ ምሥጢር፣ ማለትም፣ በማንኛውም ዓይነት ከባቢ ሁኔታ፣ የግል ሁኔታ ወይም አጋጣሚ ከተፈጥሯዊ ሕይወታችን በገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ እንደ መለወጥ ምሥጢር መማር ያስፈልገናል (ፊልጵ. 4፡12)፤ ይህ ተግባራዊ እና ቀላል ምሥጢር ያለው በቁጥር 6 እና 7 ነው—"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።"

III. **"በየዕለት ሕይወታችን ችግሮች ሲኖሩን፣ ከሌሎች ምክር መፈለግ የለብንም፣ ምክንያቱም በውስጣችን መንፈስ አለን፤ በመንፈሳችን ውስጥ እንደ መንፈስ የሚኖረው ጌታም ለእኛ በጣም ቅርብ ነው። ስልክ ወይም የፋክስ ማሽን መጠቀም ሳያስፈልገን ስለ ሁሉም ነገር ልንጠይቀው እንችላለን፣ ምክንያቱም እርሱ በውስጣችን ከእኛ ጋር መነጋገር ይችላል። በሁሉም ነገር ከእርሱ ጋር መነጋገር እና መመካከር ትችላላችሁ። የጌታ ቃል "በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ" ይላል (ፊልጵ. 4፥6)። ስለዚህ፣ አንዳች ችግር ቢኖራችሁ፣ ለእርሱ መንገር ብቻ ያስፈልጋችኋል። እርሱ በውስጣችሁ ነው፣ ከእናንተም ጋር ፊት ለፊት ነው። ሦስታንዱ አምላክ—አብ፣ ወልድ እና መንፈስ—በውስጣችን ያለው ሊያስቸግረን ሳይሆን ጠበቃችን፣ አጽናኛችን እና ደጋፊያችን ለመሆን ነው። ሁልጊዜ "ጌታ ሆይ፣ አሁን ልራመድ ነው። ደግፈኝ፣ አስቀጥለኝ እና አጠንክረኝ" ብዬ እጸልያለሁ። ይህ ጌታን መጠጣት ነው። በዚህ መንገድ ምንም ጭንቀት የለኝም። ጭንቀት ሲመጣ "ጌታ ሆይ፣ ይህ ጭንቀት የአንተ ነው፣ የኔ አይደለም፤ ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ ምክንያቱም አንተ ትሸከምልኛለህ" ማለት አለባችሁ። በዚህም፣ የጌታን ንጥረ-ነገር ወደ ውስጣችሁ ተቀበላላችሁ፣ ገንባ-አፍራሽ ቅንባሮም በውስጣችሁ ያለማቋረጥ ይሠራል። ከዚህም የተነሣ፣ በውጫዊ መንገድ በእናንተ በኩል የሚገለጠው ክርስቶስ ነው። ክርስቶስን መኖር ይህ ነው። <u>ይህንን ምሥጢር የማያውቁ ክርስቶስን መኖር</u> <u>ከባድ ነገር እንደሆነ ያስባሉ። በእርግጥ፣ ያለማቋረጥ ከጌታ ጋር መነጋገርን በተግባር መለማመድ ብቻ ያስፈልጋችኋል። ያኔ፣</u> <u>በቅጽበት ክርስቶስን ትኖራላችሁ</u>።"—The Organic Aspect of God's Salvation, pp. 54-55፦**

ሀ. ክርስቶስ ራሱ የሰውን ሁሉ አእምሮ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ነው—ፊልጵ. 4፥7፤ ኢሳ. 9፥6፤ የሐ. 14፥27፤ ሉቃ. 7፥50፤ ሮሜ 3፥17፤ 5፥1፤ 8፥6፤ 15፥13፤ 16፥20።

ለ. በነገር ሁሉ የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በየዕለቱ የሚከሰቱብንን የተለያዩ ነገሮችን ነው፤ ጸሎት አምልኮን እና ኅብረትን እንደ ውስጠ-ነገሩ በመያዝ አጠቃላይ ነው፣ ልመና ለልዩ ፍላጎቶች በመሆኑ የተለየ ነው፤ ጸሎታችን እና ልመናችን ሁለቱም ለጌታ ምስጋናን በመስጠታችን መታጀብ አለባቸው—ፊልጵ. 4፥6።

ሐ. ለእግዚአብሔር የሚለው በሕያው ጥምረት እና በጋራ ተሳትፎ፣ ኅብረትን በማመልከት ወደ እርሱ መሄድን ያመለክታል፤ ስለዚህ፣ እዚህ ጋር ለእግዚአብሔር የሚለው ትርጉም "ከእግዚአብሔር ጋር በሚደረግ ኅብረት ውስጥ" ማለት ነው—ቁ. 6።

መ. በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግን በተግባር የመለማመድ ውጤቱ የእግዚአብሔርን ሰላም መደሰታችን ነው፤ በእርግጥ፣ የእግዚአብሔር ሰላም፣ ከእርሱ ጋር በጸሎት በምናደርገው ኅብረት አማካይነት እግዚአብሔር እንደ ሰላም (ቁ. 9) ለችግሮች እና ለጭንቀት እንደሚሆን ማርከሻ ወደ ውስጣችን መስረጹ ነው (ዮሐ. 16፥33)።

ሠ. የሰላም አምላክ ልባችንንና ኃሳቦቻችንን በክርስቶስ ባለማቋረጥ እየቃኘ ይጠብቃል፣ የተረጋጋን እና በዕረፍት የተሞላን እንደንሆን ያደርገናል (ተዛ. ኢሳ. 30፥15)፤ ከጭንቀት ነጻ የሆነ ሕይወት እንዲኖረን ከፈለግን፣ ሁኔታዎቻችን ሁሉ፣ ጥሩዎቹም ይሁኑ መጥፎዎቹ፣ ክርስቶስን ማትረፍ፣ ክርስቶስን መኖር እና ክርስቶስን ማጉላት የሆነው ዕጣ ፈንታችንን በመፈጸም እኛን ለማገልገል በእግዚአብሔር የተወሰኑልን መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልገናል (ሮሜ 8፥28-30፤ ማቴ. 10፥29-31፤ 2 ቆሮ. 4፥15-18)።

## IV. "በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ [ክቡር የሆነውን] ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ"— ፊልጵ. 4፥8፦

ሀ. እነዚህ ሰናይ ባሕርያት የእግዚአብሔር አካል መልበስ የሆነውን ክርስቶስን ከሚከታተሉ ውስጥ የእግዚአብሔር ባሕርያት የመኖራቸው መገለጦች ናቸው።

ለ. እነዚህ ሰናይ ባሕርያት ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ስድስት ገጽ ገጽታዎች ናቸው፦፥

1. ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት እውነት ነው—በስነ ምግባር እውነተኛ፣ ማስመሰል ወይም ውሸት የሌለው ነው።
2. ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት የተከበረ ነው—ክብረት ያለው፣ ከፍተኛ የሥነ ምግባር ደረጃ ያለው፣ ክብደት ያለው፣ ጠንካራ፣ ሚዛን የሚደፉ እና አክብሮት የሚገባው ነው—1 ጢሞ. 3፥8፣ 11፤ ቲቶ 2፥2፤ ተዛ. ሮሜ 9፥21።
3. ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ጻድቅ ነው—በእግዚአብሔር እና በሰው ፊት ትክክል ነው—ፊልጵ. 3፥9።
4. ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ንጹሕ ነው—በውጥኑ እና በተግባሩ ነጠላ፣ ድብልቅ የሌለው ነው—ማቴ. 5፥8።
5. ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት የሚወደድ ነው—ተወዳጅ፣ ተስማሚ እና ተፈቃሪ ነው።
6. ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት በመልካም የሚወራለት ነው—ዝነኛ፣ መልካም ስም ያለው፣, የሚስብ፣ የሚያሸንፍ እና ቸር—ሆሴ. 14፥7።

ሐ. በጎነት እና ውዳሴ፣ በቀደሙት ስድስት ነገሮች በሁሉም ውስጥ አንዳች በጎነት እና ልህቀት፣ ውዳሴ የሚገባውም ነገር ያለባቸው የቀደሙት ስድስት ነገሮች ድምር ናቸው—ማቴ. 5፥16።

መ. ተገቢ ሰው መሆን ማለት፣ እንደ እግዚአብሔር ባሕርያት እውነታ በክርስቶስ የተሞላ የስብዕና ሕይወት ያለን እንሆን ዘንድ በስብዕና ሰናይ ባሕያችን ውስጥ ባሉት መለኮታዊ ባሕርያቱ በኩል እግዚአብሔርን መግለጥ ነው—ተዛ. ዘፍ.1፥26።

## V. "የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና። መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ"—ፊልጵ. 4፥11-13፦

ሀ. ጳውሎስ ከክርስቶስ የተነሣ በሁሉም ዓይነት አጋጣሚ፣ በማንኛውም ሁኔታ እና በማንኛውም ጉዳይ በክርስቶስ በመርካት እና በመደሰት ክርስቶስን እንደሚለማመድበት ምሥጢር ክርስቶስን ወሰደው—ቁ. 4።

ለ. ምሥጢሩን ተምሬአለሁ በቀጥታ ሲተረጎም "እንድገባ ተደርጌአለሁ" ማለት ነው፤ እዚህ ጋር ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር አንድ ሰው በመሠረታዊ መርሆቹ ውስጥ መመሪያዎች ወዳሉት ወደ ምሥጢር ማኅበረሰብ ውስጥ እንዲገባ መደረጉን ያመለክታል—ቆላ. 2፥2፤ ኤፌ. 3፥3-4፤ 5፥32፦

1. ጳውሎስ ክርስቶስን ወደ ማመን ከተለወጠ በኋላ፣ ወደ ክርስቶስ ውስጥ እና ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል—ሐዋ. 9፥3-19፣ 25-28፤ 22፥6-21፤ 13፥1-4።
2. ጳውሎስ ክርስቶስን እንዴት እንደ ሕይወቱ እንደሚወስድ (ቆላ. 3፡4)፣ ክርስቶስን እንዴት እንደሚኖር (ፊልጵ. 1፡ 21)፣ ክርስቶስን እንዴት እንደሚያጎላ (ቁ. 20)፣ ክርስቶስን እንዴት እንደሚያተርፍ (3፥8፣ 12) እና የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንዴት እንደሚኖረው (1፥8፣ 19፤ 2፥1-4፣ 19-20፤ 4፥1-3) ምሥጢሩን ተማረ።
3. በፊልጵስዩስ 4 ያለው ምሥጢር ኃይልን እንደሚሰጠን ማንነት በክርስቶስ ሁሉን ማድረግ ነው (ቁ. 13፤ ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ #564)፤ በክርስቶስ ውስጥ እንዳለ ሰው፣ ጳውሎስ ክርስቶስን በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ተለማመደው፣ ተገበረውም (ፊልጵ. 3፥9)፤ ይህ ክርስቶስ እውን፣ ሕያው፣ ቅርብ፣ የሚገኝ እና አሸናፊ ነው (4፥5፤ ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ #539)።
4. ክርስቶስ ኃይል ሰጪ ስለመሆኑ ጳውሎስ የተናገረው ቃል፣ እንደ ሰናይ ባሕርያታችን እርሱን እንድንኖረው እና በዚያም ወሰን-በሌለው ታላቅነቱ እንድናጎላው ክርስቶስ ለእኛ ኃይል በመስጠቱ ላይ በተለየ መልኩ የሚተገበር ነው—ፊልጵ. 4፥8-13።
5. በክርስቶስ ኃይል መስጠት አማካይነት፣ የረካ ሕይወትን መኖር እና እውነተኛ፣ የተከበርን፣ ጻድቅ፣ ንጹሕ፣ የምንወደድ እና መልካም የሚወራልን መሆን እንችላለን (ቁ. 11-12፣ 8)፤ የእነዚህን ሰናይ ባሕርያት ሕይወትን መኖር የክርስቲያን ሥራን ከመሥራት ይልቅ ይበልጥ ከባድ ነው።
6. ክርስቶስን ኃይል እንደሚሰጠው ማንነት መለማመድ ከፈለግን፣ በሚከተሉት ጉዳዮች ከእርሱ ጋር መተባበር ያስፈልገናል፦
   - ሀ. በምድር ላይ ባለ ተግባራዊ ኑሮአችን፣ ወደ እግዚአብሔር ፊት በመምጣት፣ ወደ እርሱ በመግባት እና በፊቱ ብርሃን በመኖር ያለማቋረጥ የሚጸልዩ ሰዎች መሆን አለብን—መዝ. 42፥5፣ 11፤ 80፥1፣ 3፣ 7፣ 19።
   - ለ. በመስቀል ላይ በፈሰሰው በጌታ ደም ላይ በመመሥረት የኃጢአቶቻችንን ጥልቅ-ዝርዝር እና ትኩስ ይቅርታ መለማመድ ያስፈልገናል—ዕብ. 9፥14፣ 10፥19፣ 22፤ ዘጸ. 24፥8፤ ማቴ. 26፥28።
   - ሐ. ዕርገት ምን እንደሆነ እና የተቀበልነው ሕይወት ሰማያዊ ሕይወት እንደሆነ ማወቅ ያስፈልገናል፤ ከጌታ ጋር ወደ ሰማያት የማረጋችንን ሃቅ እና ከዚህም የተነሣ ሰማያዊ ሰዎች መሆናችንን ማወቅ አለብን፤ በውጫዊ መንገድ፣ አሁንም በምድር ላይ እየኖርን ነው፣ ነገር ግን በውስጣዊ መንገድ፣ ከውስጥ ሕይወታችን እና ሁኔታ አኳያ፣ በሰማያት እየኖርን ነው—ኤፌ. 2፥6፤ ዕብ. 8፥1-2፤ 4፥14-15፤ 7፥25-26።

**መልእክት አራት የቡድን የንባብ ክፍል**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- **ፊልጵ. 4፥5-9፣ 11-13**

በፊልጵስዩስ 1፥21 ጳውሎስ፣ "ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ" ነው በማለት ያውጃል። ይህ ዓረፍተ ነገር፣ የጳውሎስ ውስጣዊ እውነታ ምስክርነት ነው። ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት እውነተኛ መገለጫ ታዲያ ምንድን ነው? ይህ መገለጫ፣ በ4፥5-9 በተዘረዘሩ ሰናይ ባሕርያት ውስጥ ይገኛል። በተመሳሳይ መርህ፣ በምዕራፍ 2 ጳውሎስ ክርስቶስን እንደ ምሳሌ ያቀርብልናል።...በዚህ ምሳሌ መሠረት የሚኖር ሕይወት መገለጫስ ምን ዓይነት ነው? መገለጫው በ4፥5-9 ይገኛል። በምዕራፍ 3 ክርስቶስን ለማግኘት ሁሉን ነገር እንደ ጉዳት፣ እንደውም እንደ ጉድፍ መቁጠርን በተመለከተ ያለው የጳውሎስ ቃልም እንዲሁ መገለጫው ነው። አንድ ሰው ፍልስፍናን ከኮነነ፣ ባሕልን ከገፋ እና ሃይማኖትን ከተወ፣ ክርስቶስንም ያገኝ ዘንድ እንደ ጉዳት ከቆጠራቸው፣ በሕይወቱ ምን ዓይነት መገለጫ ይኖራል?...አሁንም...መገለጫው በ4፥5-9 መታየት ይችላል። (Life-study of Philippians, p. 222)

ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት መገለጫ የመጀመሪያ ገጽታ ገርነት ነው (ፊልጵ. 4፥5)።... ሁለተኛው ገጽታ ጭንቀት አልባነት ነው። ክርስቶስን በሚኖር ሕይወት ገርነት እንጂ ጭንቀት፣ ስጋት የለም...ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት የተረጋጋ፣ የሰከነ፣ ሰላማዊ እና ጸጥተኛ ነው። በተቃራኒው፣ የተረበሸ ሕይወት ሰይጣንን የሚኖር ሕይወት ነው። ገርነት፣ ለሰከነና ለተረጋጋ ሕይወት እጅግ አስፈላጊው ንጥረ ነገር ነው። ገርነት፣ ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ያለን ፍትሐዊነትና አሳቢነት ነው። ገርነት ያለው መሆን ማለት፣ ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ሕጋዊ ሙብትን አለመጠየቅ ማለት ነው።

ገርነት፣ ትዕግስትንና ልከኝነትን ያካትታል፤ ከዚህም ግን ያልፋል። ገርነት ካለችሁ፣ ከሌሎች ጋር አትጨቃጨቁም፤ ከሌሎች ጋር አትፋለሙም ወይም ከእነርሱ ጋር አትከራከሩም። ብዙ የምትሉት ይኖራችሁ ይሆናል፤ ነገር ግን ከሌሎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት ትዕግስት እና ልከኝነት ይኖራችኋል፤ ለማስቆጣታቸው ወይም ለማበሳጨታቸው ምንም ምላሽ አትሰጡም።

የተወሰኑ እኅቶች በጋራ እየኖሩ ነው እንበል። እጅግ ውድ የሆነችው እኅት ከሁሉ በላይ ገር የሆነችው ናት። አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣ የተረጋጋችና ጸጥታኛ ትሆናለች። ሌሎች ቢበድሏት እንኳ፣ መልሳ አታጠቃቸውም። ገርነት የሌላቸው እኅቶች ግን፣ ሲበደሉ በቀላሉ መልስ ይሰጣሉ...ተገቢ የክርስትና ሕይወት የተረጋጋ ሕይወት ነው። እንደዚህ ዓይነቱን ሕይወት መኖር ማለት፣ ከሰዎች ጋር አንጨቃጨቅም ወይንም ከእነርሱ ጋር አንፋለምም ማለት ነው።

ገርነት፣ ጳውሎስ ከጠቀሳቸው ከሁለቱ አሉታዊ ነገሮች፣ ከራስ ወዳድነት ምኞት እና ከከንቱ ውዳሴ በተጻራሪ ነው (ኢ.መ.ት) ። ገርነት ከማጉረምረም እና ከመከራከር በተቃራኒ ነው።...የራስ ወዳድነት ምኞት፣ ከንቱ ውዳሴ፣ ማጉረምረም እና ክርክር በእኛ ዘንድ ሲኖር፣ መረጋጋት፣ መስከን፣ ገርነት አይኖርም።

ክርስቶስን ከኖርን፣ ከሌሎች ጋር አንጨቃጨቅም። መናገር የምንችልበትን፣ የሚያረጋጋን ቃል እንኳን ልንናገር የምንችልበትን ትክክለኛውን ጊዜ እናውቃለን። በተሳሳተ ጊዜ የተነገረ የሚያረጋጋ ዓረፍተ-ነገር እንኳ ለጭቅጭቅ ይዳርጋል...የሆነ ሰው ከተናደደባችሁ፣ ምንም አለማለት እጅግ የተሻለ ነው። ገርነትን አንቀሳቅሱ፤ ተገቢ ቃል ለመናገርም ትክክለኛውን ጊዜ ጠብቁ። ይህ በተለይም ላገቡ ወንድሞችና እኅቶች አስፈላጊ ነው። ባለችሁ ወይም ሚስታችሁ ተጨቃጫቂ ከሆነች፣ ስለምትናገሩበት መንገድ ተጠንቀቁ። ጌታን ጮኽ ብሎ አለመጥራት እንኳ ጥበብ ሊሆን ይችላል። እንደዚያ ዓይነቱ መጥራት ችግርን ሊያመጣ ይችላል። ውጫዊ በሆነ መንገድ በመናገር ፈንታ፣ ራሳችሁን አረጋጉ፤ በውስጥ ጌታን ጥሩት፤ የሆነን ነገር ከመናገራችሁም በፊት ሁኔታው እስኪረጋጋ ድረስ ጠብቁ።

በዕድሜ እንደገፋ ሰው፣ በሰብዕና ሕይወት እጅግ አያሌ በሆኑ ልምምዶች አልፌአለሁ። በጌታ ሉዓላዊ እጅ ሥር፣ በብዙ የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ነበርሁ። ድህነትን አውቃለሁ፤ የፍላጎቶቼ መሟላትም ምን እንደሆነ አውቃለው። በሰብዕና ሕይወት ሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ፣ ጭንቀት እንዳለ መመስከር እችላለሁ። ጭንቀት የሰብዕናን ሕይወት ጠቅልሎ የሚይዝ ቃል ነው። የሰብዕና ሕይወት ጥቅል ድምር ጭንቀት ነው።

ጳውሎስ በ4፥6 ስለ ጭንቀት ይናገራል፤ ምክንያቱም ጭንቀት የሰው ሕይወት ጥቅል ድምር እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። እንዲሁ ደግሞ ገርነት፣ የተገቢው የክርስትና ሕይወት ጥቅል ድምር መሆኑን ተገንዝቧል...ስለዚህ፣ ክርስቶስን መኖር ገርነት ያለን፣ ጭንቀት አልባ መሆን ነው። (Life-study of Philippians, pp. 223-224, 513)

በቃል ጥናቱ ዉኤስት (Wuest) የተሰኘው ሰው፣ "ገርነት" ለሚለው የግሪኩ ቃል፣ ከሚገባን በታች በሆነው መርካት ብቻ ሳይሆን ጣፋጭ ምክኒያታዊነት ማለት ጭምር እንደሆነ ያመለክታል። ቃሉ ራስን መግዛትን፣ ትዕግስትን፣ ልከኝነትን፣ ቸርነትን እና መረጋጋትን ያካትታል። በተጨማሪም፣ በክርስትና ልምምድ መሠረት፣ ገርነት ሁሉን- ያካተተ ነው፤ ምክንያቱም የክርስትናን ሰናይ ባሕርያት ሁሉ የሚያካትት ነው። ይህ ማለት፣ ገርነትን ማሳየት ካልቻልን የትኛውንም የክርስትና ሰናይ ባሕርይ ማሳየት አልቻልንም ማለት ነው...በክርስቶስ ጸጋ፣ አንድ ወንድም ከሚገባው በታች በሆነ ነገር ቢረካና ሚስቱን ባለመንቀፍ ወይም ባለመኮነን ለእርሷ ገርነትን ቢያሳይ፣ በገርነቱ ሁሉን-ያካተተ የክርስትናን ሰናይ ባሕርያት ያሳያል። ገርነቱ ትዕግስትን፣ ትሕትናን፣ ራስን መግዛትን፣ ወደ ጌታ መመልከትን ብሎም በሁሉም ነገር ጌታ ሉዓላዊ መሆኑን የመቀበልን ሰናይ ባሕርይ የሚያካትት ይሆናል። (Life-study of Philippians, pp. 479-480)

አንዳንድ ጊዜ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የምንኖርበት ምክንያቱ፣ ገርነት ስለሌለን ነው። እንዲሁም፣ አሉታዊ አመለካከቶችና መልካም ያልሆኑ ቃላት የሚመጡት ከገርነት እጥረት ነው። መውደድ ካቃተን፣ ምክንያቱ ገርነት ስለሌለን ነው። በተመሳሳይ፣ ታጋሽ ያልሆንነው ገርነት ስለሚያጥረን ነው። ለፍላፊነትም እንኳን ገርነት ከማጣት የሚመጣ ሊሆን ይችላል... ለቤተሰባችን አባላት ገርነትን ካላሳየን፣ በቤተሰብ ሕይወታችን ሰላም አይኖረንም። ሰላም የሚመጣው ከገርነት ነው።

ጳውሎስ፣ ገርነት ሁሉን ያካተተ ሰናይ ባሕርይ እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። "ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ" (ፊልጵ. 4፥5) ያለበትም ምክንያት ይህ ነው። ይህ ገርነት፣ በእርግጥ ክርስቶስ ራሱ ነው። ጳውሎስ በ1፥21፣ "ለእኔ መኖር ክርስቶስ ነው" ይላል (አ.መ.ት)። ክርስቶስ ገርነት ስለሆነ፣ ለጳውሎስ መኖር ገርነት ነበር። ጳውሎስ የሚናፍቀው ነገር፣ በሕይወት ወይም በሞት የክርስቶስን በእርሱ መጉላት ነበር። ለጳውሎስ፣ ክርስቶስን ማጉላቱ ገርነቱን ማሳየቱ ነበር። ስለዚህ፣ ክርስቶስ በእኛ መጉላቱ፣ ገርነታችንን ለሰው ሁሉ ከማሳወቃችን ጋር እኩል ነው። የዚህም ምክንያት፣ ገርነት በተግባራዊ መንገድ የተለማመድነው ክርስቶስ ስለሆነ ነው። ክርስቶስን ስለመኖር ልንናገር፣ እንዲሁም ለእኛ መኖር ክርስቶስ እንደሆነ ልንመሰክር እንችላለን። ሆኖም፣ ቀን በቀን በቤታችን ላለን ሕይወት የሚያስፈልገን ገርነት ነው። ገርነት ካለን፣ ያን ጊዜ በልምምዳችን ክርስቶስ የእውነት ይኖረናል።

ጥሩ ባል ወይም ሚስት ለመሆን ቁልፉ ገርነት ነው። በድጋሚ ለመናገር፣ ገርነት የተረጋጉ ወይም ትሑት ከመሆን የላቀ ነው። ሁሉን እንዳካተተ የክርስትና ሰናይ ባሕርይ፣ ገርነት ክርስቶስ ራሱ ነው። በቤተሰብ ሕይወታችን እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን በሁለቱም፣ የገርነት ሕይወት በመኖር ክርስቶስን መኖር ያስፈልገናል።

የገርነትን ትርጉም ይበልጥ ስናጤነው፣ ጳውሎስ በ4፥5 ስለ ገርነት የተናገረበትን ምክንያት እናደንቃለን። በክርስትና ሕይወታችን ያሉ ውድቀቶቻችንና እጦረቶቻችን የሚመጡት ገርነት ስለሌለን ነው። ሁሉም ቅዱሳን፣ ወጣቱና ሽማግሌው በተመሳሳይ፣ ገርነትን ቸል የማለት ዝንባሌ አላቸው። ክርስቶስን መኖር ከፈለግን፣ ከሚገባን በታች ስናገኝ መርካት አለብን። በሌሎች ላይ ከባድ ሸክም መጫን የለብንም።

ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ የገርነትን ሕይወት ኖሯል። በአንድ በኩል ጥብቅ ነበር፤ በሌላ በኩል ግን፣ እጅግ ታጋሽ ነበር። ለምሳሌ፣ እጅግ ብዙ የሚጸልይ ቢሆንም እንኳን፣ ስለ ጸሎት በደቀ መዛሙርቱ ላይ ሸክምን አልጫነም ወይንም በበቂ ስላልጸለዩ አልኮነናቸውም።

ጳውሎስ ስለ ገርነት ከተናገረ በኋላ ወዲያውኑ "ጌታ ቅርብ ነው" በማለት ይቀጥላል... ከልምምድ አንጻር...ይህ ቃል ዛሬ ከእኛ ጋር ያለውን የጌታን መገኘት እንደሚያመለክት መናገር እችላለሁ። ለሰዎች ሁሉ ገርነታችንን እንድናሳይ የሆነውን የጳውሎስን ምክርም ያጠነክራል። ጌታ ቅርብ ስለሆነ፣ ገርነታችንን ላለማሳየት ምንም ማመካኛ የለንም። ብዙ ጊዜ ጌታ ቅርብ እንደሆነ ስለምንረሳ፣ ገርነታችንን አናሳይም። በእርግጥ በውስጣችን እንዳለ አንኳን ትዝ አይለንም።...ጌታ ቅርብ እንደሆነ ስላልተገነዘብን፣ ገርነታችንን አናሳይም። (Life-study of Philippians, pp. 480-481)

ገርነት ለሚለው የግሪኩ ቃል..."ፍትሐዊ፣ አሳቢ፣ ምቹ እና የሚገጥም" ማለት ነው። ገር የሆነ ሰው ሁልጊዜ የሚገጥም፣ ባሕርይው ሁልጊዜም የሚስማማ ሰው ነው። አንዳንድ ቅዱሳን መልካም ናቸው፤ የሚገጥሙ ግን አይደሉም። ከቦታ ወደ ቦታ ሊጓዙ ይችላሉ፤ ነገር ግን የትም ቢሄዱ፣ ደስተኞች አይደሉም። እነዚህ ቅዱሳን ከሰው የማይገጥሙበት ምክንያት ገር ስላልሆኑ ነው። ገር የሆነ ሰው፣ ሁኔታዎች ወይም ከባቢ ሁኔታ ምንም ቢሆን ሁልጊዜ የሚገጥም፣ ባሕርይው ሁልጊዜ ምቹ የሆነ ሰው ነው። (Life-study of Philippians, pp. 489-490)

ገርነት ሰላማዊነትን፣ ትሕትናን እና መረጋጋትን ጭምር ያካትታል። ፍትሐዊ፣ አሳቢ እና መግጠም የምትችሉ ከሆናችሁ፣ ያለጥርጥር የተረጋጋችሁ፣ ቸር፣ ትሑት እና ሰላማዊ ናችሁ። የዋህና ልከኛ፣ ለሌሎችም በርኅራኄ የተሞላችሁ ጭምር ትሆናላችሁ...የገርነት ተቃራኒው ያለ ምሕረት በሰዎች ላይ መጠይቅን ማኖር ነው። ገርነት የሚያጥረው ሰው ምሕረት የለሽ እና በሌሎች ላይ ሸክምን የሚጭን ነው። ገር መሆን ማለት ግን የሚገባንን ባናገኝም እንኳን እንረካለን ማለት ነው...ለምሳሌ፣ አንድ ነገር የእኛ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ጥብቅ በሆነ ሕጋዊ መብት መሠረት የእኛ እንደሆነ አንሚገትም። ይህ ገርነት ነው።

የጌታ ኢየሱስ ሕይወት የገርነት ምርጥ ምሳሌ ነው። ወደ ኤማሁስ ሲሄዱ ከነበሩት ከሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጋር እንዴት እንደተነጋገረ አገናዝቡ። ሉቃስ 24፥15 (አ.መ.ት)፣ እነዚህ ደቀ መዛሙርት "እየተነጋገሩና እየተወያዩ ሳሉም ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋራ ይሄድ ጀመር፤" ይላል። ጌታ ኢየሱስም፦ ""እየሄዳችሁ፣ መንገድ ላይ እርስ በርስ እንዲህ የምትወያዩት ምንድን ነው?" አላቸው።" እነርሱም "በሐዘን ክው ብለው ቆሙ" (ቁ. 17)። በቁጣም ከደቀ መዛሙርቱ አንደኛው፣ ""በእነዚህ ቀናት እዚህ በኢየሩሳሌም የሆነውን ነገር የማታውቅ፣ አንተ ብቻ ለአገሩ እንግዳ ነህን?" ሲል መለሰለት" (ቁ. 18)። ምን እንደተከናወነም የማያውቅ በመምሰል፣ ጌታም "የሆነው ነገር ምንድን ነው?" ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም "በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ" ማብራራታቸውን ቀጠሉ። የካህናት አለቆችና መኳንንቶችም ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት መናገራቸውን ቀጠሉ። ከእነርሱ ይልቅ የሚያውቀውን ነገር ደቀ መዛሙርቱ ሲናገሩ ለመስማት ጌታ እንዴት ገር ነበር! ረዥም መንገድ ከተጓዙ በኋላም፣ "ወደሚሄዱበትም መንደር በተቃረቡ ጊዜ፣ ኢየሱስ ዐልፎ የሚሄድ መሰለ" (ቁ. 28)። "እነርሱ ግን...አጥብቀው ለመኑት፤ ስለዚህ ከእነርሱ ጋራ ለማደር ገባ" (ቁ. 29)። ከእነርሱ ጋር ለመብላትም በማዕዳቸው ተቀመጠ። እንጀራውን ባነሣ፣ በባረከው፣ ቆርሶም በሰጣቸው ጊዜ፣ "ዐይናቸው ተከፈተ፤ ዐወቁትም" (ቁ. 31)። በነዚህ ሁሉ፣ የጌታን ገርነት እናያለን።

ከጌታ ኢየሱስ ውጭ፣ ይህን የገርነት ሕይወት በተግባር የተለማመደ አንድም የሰው ልጅ የለም። የታዋቂ ሰዎችን የሕይወት ታሪክ ብታጠኑ፣ አንዳቸውም በእውነት ገር ሰዎች እንዳልሆኑ ታያላችሁ። አራቱን ወንጌላት ካነበባችሁ ግን፣ የጌታ ኢየሱስ የሰብዕና ሕይወት በገርነት የተሞላ እንደነበር ታያላችሁ።

በገርነት የተሞላውን ሕይወት የኖረው ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው፤ ዛሬ ፍጹም ገርነታችን ሊሆን የሚችለውም ክርስቶስ ብቻ ነው። የክርስቶስን የሰብዕና ሰናይ ባሕርያት ጥቅል ድምር የሚያጠቃልለው ቃል፣ ገርነት ነው። ገርነታችንን ማሳየት ማለት ክርስቶስን የሚገልጥ ሕይወት መኖር ማለት ነው፤ በእርሱ አማካኝነት የምንኖረውን ክርስቶስ መግለጥ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት፣ እንደ ሁሉም የሰብዕና ሰናይ ባሕርያት ጥቅል ድምር ክርስቶስ ራሱ ነው።

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 4፥5፣ “ጌታ ቅርብ ነው” ይላል።...እርሱ ከእኛ ጋር ነው። እርሱን እንደ ምሳሌያችን በመውሰድና እርሱን እናገኘው ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ በመቁጠር እርሱን ከኖርን፣ እርሱ ከእኛ ጋር እንዳለ ይሰማናል። በስፍራም በጊዜም እርሱ ቅርብ ነው። ከቦታ አንጻር፣ ለእኛ ቅርብ ነው፤ ሊረዳንም ዝግጁ ነው። ከጊዜ አንጻር፣ እርሱ በደጅ ነው፤ በቅርቡም ይመጣል። ጌታ ቅርብ ከሆነ፣ መቸገርና መናወጣችን ለምንድን ነው? (Life-study of Philippians, pp. 490-492, 224-225)

በፊልጵስዩስ 4፥6 ጳውሎስ ስለ ጸሎት፣ ስለ ልመና እና ስለ ምስጋና ይናገራል። ጸሎት አጠቃላይ ሲሆን የአምልኮና የኅብረትን ውስጠ-ነገርም የሚያካትት ነው፤ ልመና ልዩ ለሆኑ ፍላጎቶች በመሆኑ የተለየ ነው...በየዕለቱ ጌታን ለመገናኘት፣ ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ እና እርሱን ለማምለክ ጊዜ ያስፈልገናል። ኅብረት እያደረግን ሳለ፣ የምንጠይቀው ልዩ የሆነ ነገር ሊኖረን ይችላል። ስለሆነም፣ ጠቅላላ በሆነ መንገድ መጸለይ ብቻ ሳይሆን፣ በተለየ መንገድም ልመናችንን ለጌታ እናቀርባለን።

ጸሎታችን እና ልመናችን፣ ሁለቱም ምስጋናን ለጌታ ከማቅረባችን ጋር መሆን አለባቸው። በቅርቡ፣ ጌታን አመስጋኝ መሆን እንዳለብኝ ደግሜ ተምሬያለሁ። ጌታ ጤናዬን እንዲመልስልኝ ስጠይቀው ሳለ፣ አሁን እንኳን ስላለኝ ጤና ባለማመስገኔ ተወቅሻለሁ። በምንታመምበት ጊዜ ሁሉ እንዲህ ልንለው ያስፈልጋል፦“ጌታ ሆይ፣ በተወሰነ መጠን ጤናማ ስለሆንኩ አመሰግንሃለሁ። ጌታ ሆይ፣ ታምሜአለሁ፤ ነገር ግን ክርስቶስን ለቅዱሳን ማገልገል እስከማልችልበት መጠን ግን አይደለም። ሙሉ በሙሉ ጤናማ እንዳልሆንኩ ግን ጌታ ሆይ ታውቃለህ። ስለዚህ፣ ጤናዬን እንድትመልስልኝ እና ሙሉ በሙሉ ጤናማ እንድታደርገኝ ደግሜ እጠይቅሃለሁ።” ሁላችንም ጌታን በዚህ መንገድ መለመንን መማር ያስፈልገናል። (Life-study of Philippians, pp. 529-530)

በፊልጵስዩስ 4፥6 ጳውሎስ...“በአንዳች አትጨነቁ” ይላል...ጭንቀት ክርስቶስን የመኖራችንን ሕይወት ይሸረሽረዋል። በመጨነቅ ፈንታ፣ በነገር ሁሉ በጸሎትና በልመና ከምስጋና ጋር፣ ልመናችንን በእግዚአብሔር ዘንድ ማስታወቅ አለብን። የእግዚአብሔርም ሰላም ልባችንንና አሳባችንን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል (ቁ. 7)። የእግዚአብሔር ሰላም ከስጋትና ከጭንቀት ያድነናል።...ከጭንቀት ነፃ መሆን እኛን የተረጋጋንና የሰከነን አድርጎ ለመጠበቅ ዓላማ ነው።

በቁጥር 6...በነገር ሁሉ የሚሉት ቃላት፣ ቀን በቀን በእኛ ላይ የሚከሰቱ የተለያዩ ነገሮችን ያመለክታሉ። ከጌታ በረከት ሥር፣ ብዙ አዎንታዊ ነገሮች ይከሰታሉ፤ መልካም ዜናዎችንም እንሰማለን። ሆኖም፣ አሉታዊ ነገሮችንም እንለማመዳለን፤ መጥፎ ዜናዎችንም እንሰማለን። ይሁን እንጂ፣ በነገር ሁሉ በጸሎትና በልመና ከምስጋና ጋር፣ ልመናችንን በእግዚአብሔር ዘንድ ማስታወቅ አለብን።

“በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ” የሚለውን የጳውሎስን ቃል መረዳት ቀላል ይመስላል...በእግዚአብሔር ዘንድ የሚለውን ሐረግ ለማጥናት ብዙ ጊዜ አጥፍቻለሁ። “በእግዚአብሔር ፊት” ወይም “በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ” ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። ብዙውን ጊዜ “ጋር” ተብሎ ለሚተረጎመው የግሪኩ መስተዋድድ ፕሮስ (pros) ነው (ዮሐ. 1፥1፤ ማር. 9፥19፤ 2 ቆሮ. 5፥8፤ 1 ቆሮ. 16፥6፤ 1 ዮሐ. 1፥2)። ኅብረትን በማመልከት፣ በሕያው ጥምረት እና ግንኙነት ወደ [እግዚአብሔር] መሄድን ያመለክታል...እንደዚህ ባለ ኅብረት፣ እንደዚህ ባለ ጥምረትና ግንኙነት በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችንን ማስታወቅ አለብን። ይህ እግዚአብሔርን እንገናኝ ዘንድ መጸለያችንን ይጠይቃል።

ልዩ የሆነ ፍላጎት ባይኖረንም እንኳ፣ ቀን በቀን ጌታን ለማምለክና ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ የጸሎት ጊዜ ያስፈልገናል። ጌታን እያመለክንና በጸሎት ከእርሱ ጋር ኅብረት እያደረግን ሳለ፣ ከእርሱ ጋር መገናኘትን እንደሰታለን፤ ሕይወታዊ ጥምረትንም በተግባር እንለማመዳለን።

ከጌታ ጋር ሕይወታዊ ጥምረትን በተግባር የመለማመድ ውጤቱ፣ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንንና አሳባችንን በክርስቶስ ኢየሱስ መጠበቁ ነው (ፊል. 4፥7)። የእግዚአብሔር ሰላም፣ በእርግጥም በጸሎት ከእርሱ ጋር በምናደርገው ኅብረት በኩል እግዚአብሔር እንደ ሰላም (ቁ. 9) ወደ ውስጣችን መሰረጹ ነው። ይህ ሰላም ለችግሮች እና ለጭንቀት ማርከሻ ነው (ዮሐ. 16፥33)። የሰላም አምላክ ልባችንንና አሳባችንን በክርስቶስ ኢየሱስ እየቃኘ ይጠብቃል፤ ይህም የተረጋጋን እና የሰከነን ያደርገናል።

ከጭንቀት ነጻ የሆነ ሕይወት እንዲኖረን ከፈለግን፣ ሁኔታዎቻችን ሁሉ፣ መልካም ይሁኑ መጥፎ በእግዚአብሔር የተወሰኑልን መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልገናል። ሁኔታዎቻችንን በእግዚአብሔር የተወሰኑልን የመሆናቸው ግንዛቤ ከሙሉ እርግጠኝነት ጋር ሊኖረን ይገባል። ያን ጊዜ፣ ስለ አዘገጃጀቱ ጌታን ማምለክ ይቻለናል። (Life-study of Philippians, pp. 225-227, 516)

በፊልጵስዩስ 4፥8 ጳውሎስ፣ ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ስድስት ገጽ ገጽታዎችን ይሰጠናል...ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት የመጀመሪያው ገጽ ገጽታው፣ “እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ” [የሚለው] ነው። እዚህ ጋር እውነት የሚለው ቃል፣ በሃቅ እውነተኛ የመሆንን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን “በሥነ ምግባር እውነተኛ” መሆን ማለት ነው። ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት መገለጫ ውስጥ፣ ሐሰት፣ ውሸት ሊኖር አይችልም። የምናደርገው ወይም የምንናገረው ነገር ሁሉ እውነተኛ መሆን አለበት...የክርስቶስ መገለጥ የሆነው ሕይወት እውነተኛ የሆነ ሕይወት ነው።

ሁለተኛ ገጽታው፣ “ክቡር የሆነውን ነገር ሁሉ” [የሚለው] ነው። “ክቡር” ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል አክብሮትን የሚያነሣሣን እና የሚጋብዝን ክብር በማመልከት “ትልቅ አክብሮት የሚገባው፣ ከፍተኛ የሥነ ምግባር ደረጃ ያለው፣ ጭምት” ማለት ነው (1 ጢሞ. 3፥8፣ 11፤ ቲቶ 2፥2)። ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ክቡር፣ ከፍተኛ የሥነ ምግባር ደረጃ ያለው፣ ጭምት፣ የጸና፣ ክብደት ያለውና አክብሮት የሚገባው ነው። (Life-study of Philippians, pp. 229-230)

ክብደት ያላቸው ሊሆኑ የሚገባቸው በዕድሜ ትልልቅ የሆኑ ሰዎች ብቻ እንደሆኑ ማሰብ የለብንም። በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ አንድ ወጣት ወንድም እንኳን ክብር ሊኖረው ይገባል፤ ምክንያቱም በውስጡ እግዚአብሔር አለ...ክብር ያለው መሆን አስፈላጊ ሰው እንደሆንን ማስመሰል አይደለም፤ እግዚአብሔርን መኖር ነው... ክርስቶስን የያዝን ዕቃ ነን። እርሱን ከኖርን፣ እውነተኛ ክብር ይኖረናል።

በፊልጵስዩስ 4፥8 ጳውሎስ፣ "ትክክል የሆነውን ነገር ሁሉ" በማለትም ይናገራል። ይህ፣ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ፍትሃዊ የሆነውን ሳይሆን ትክክል የሆነውን የሚያመለክት ነው።

ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ በሚለው አገላለጽ ውስጥ ንጹሕ የሚለው ቃል፣ "ያለ ምንም ድብልቅ፣ በውጥንና በድርጊት ነጠላ የሆነ" ማለት ነው። በዚህ መንገድ ንጹሕ መሆን ማለት፣ ምንም ማስመሰል የሌለው መሆን ማለት ነው። ንጽሕናም እንዲሁ ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት ገፀ ገጽታ ነው።

እንዲህ ያለው ሕይወት ሌላኛው ገጽታ፣ "ተወዳጅ የሆነውን ሁሉ" [የሚለው] ነው። ተወዳጅ የሚለው ቃል "የሚወደድ፣ ተስማሚ፣ ተፈቃሪ" ማለት ነው።

በመቀጠል ጳውሎስ "መልካም የሆነውን ሁሉ" ይላል። ይህ ማለት መልካም ስም ያለውን፣ የሚስብ የሆነውን፣ የሚያሸንፍ የሆነውን ሁሉ ማለት ነው። የግሪኩ ቃል "በጎ የሆነ" የሚል ትርጉም አለው።

ክርስቶስን ከኖርነው፣ በእርግጠኝነት የእነዚህ ሁሉ ገጽታዎች መገለጫ የሆነ ሕይወት ይኖረናል። በኑሯችን ምንም ዓይነት ውሸት፣ ልቅነት ወይም ክብደት አልባነት አይኖርም። ይልቁንም፣ ኑሯችን ክቡር፣ ንጹሕ፣ ትክክል፣ ተወዳጅ እና መልካም ወሬ ያለበት ይሆናል። ከብዙዎቹ የክርስትና ሰናይ ባሕርያት፣ ጳውሎስ እነዚህ ስድስቱን እንደ ገፀ ገጽታዎች መርጧቸዋል።

ሁሉም የሰብዕና ሰናይ ባሕርያት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ነበር...ልክ ጓንት እጅን ለመያዝ በእጅ መልክ እንደተፈጠረ ሁሉ፣ የእኛም የሰብዕና ሰናይ ባሕርያት የተፈጠሩት መለኮታዊውን ሰናይ ባሕርያት ይይዙ ዘንድ እንደ መያዣ ዕቃ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መልክ ክርስቶስ እንደሆነ ይናገራል (ቆላ. 1፥15፤ 2 ቆሮ. 4፥4)...ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክ ነው ማለት፣ ሰው የተፈጠረው በክርስቶስ መልክ መሠረት ነው ማለት ነው...ሰው በእግዚአብሔር የተሠራው የክርስቶስን ምሳሌ ይይዝ ዘንድ ነው። ክርስቶስ ወደ አንድ ሰው ሲመጣ፣ ያ ሰው ክርስቶስን የያዘ መያዣ ዕቃ ይሆናል።

በፊልጵስዩስ 4፥8 መጨረሻ፣ ጳውሎስ አገላለጹን በመቀየር "በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን" ይላል። እዚህ በጎነት ለሚለው የግሪኩ ቃል "ልህቀት" ማለት ነው፤ ያም በብርቱ ተግባር የሚገለጥ ሥነ ምግባራዊ ጉልበት ነው። ምስጋና እንደ በጎነት ተጓዳኝ፣ ምስጋና የሚገባቸውን ነገሮች ያመለክታል።

በጎነትና ምስጋና ሁለት ተጨማሪ ገጽታዎች ሳይሆኑ ቀድመው የተጠቀሱት ስድስቱ ገጽታዎች እሴቶች ናቸው። በጎነት ልዩ ገጽታ ሳይሆን አጠቃላይ ቃል ነው። በእውነተኝነት፣ በክብር፣ በንጽሕና፣ በተወዳጅነት፣ በትክክልነት እና መልካም በሆነው ውስጥ በጎነት አለ። ምስጋናንም በተመለከተ መርሁ ተመሳሳይ ነው፦ በእነዚህ በስድስቱ የክርስትና ሰናይ ባሕርያት ሁሉ ውስጥ አንዳች ምስጋና የሚገባው ነገር አለ።

ክርስቶስን የሚኖር ሕይወት መገለጫ እንዴት የላቀ ነው!...በእነዚህ በላቁ ገጽታዎች በእያንዳንዳቸው ውስጥ፣ በጎነትና ምስጋና የሚገባው አንዳች ነገር አለ። "እንደ እነዚህ ስላሉት ነገሮች" ማሰብ አለብን፤ ይህም ማለት ስለ እነርሱ ማሰብ፣ ስለ እነርሱ ማሰላሰል፣ ማጤን ነው። (Life-study of Philippians, pp. 230-233)

"በየዕለት ሕይወታችን ችግሮች ሲያጋጥሙን፣ ከሌሎች ምክር መፈለግ የለብንም፣ ምክንያቱም በውስጣችን መንፈስ አለን፤ በመንፈሳችን ውስጥ እንደ መንፈስ የሚኖረው ጌታም ለእኛ እጅግ ቅርብ ነው። ስልክ ወይም የፋክስ ማሽን መጠቀም ሳያስፈልገን ስለ ሁሉ ነገር ልንጠይቀው እንችላለን፤ ምክንያቱም እርሱ በውስጣችን ከእኛ ጋር መነጋገር ይችላል። በሁሉም ነገር ከእርሱ ጋር መነጋገር እና መመካከር ትችላላችሁ። የጌታ ቃል "በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ" ይላል (ፊልጵ. 4፥6)። ስለሆነም፣ አንዳች ችግር ካጋጠማችሁ፣ ለእርሱ መንገር ብቻ ያስፈልጋችኋል። እርሱ በውስጣችሁ ነው፤ ከእናንተም ጋር ፊት ለፊት ነው። ሦስታንዱ አምላክ፣ ማለትም አብ፣ ወልድ እና መንፈስ በውስጣችን ያለው ሊያስቸግረን ሳይሆን ጠበቃችን፣ አጽናኛችን እና ደጋፊያችን ለመሆን ነው። ሁልጊዜም እንዲህ ብዬ እጸልያለሁ፣ "ጌታ ሆይ፣ አሁን ልራመድ ነው። ደግፈኝ፣ አስቀጥለኝ፣ አጠንክረኝ።" ይህ ጌታን መጠጣት ነው። በዚህ መንገድ ምንም ጭንቀት የለብኝም። ጭንቀት ሲመጣ፣ "ጌታ ሆይ፣ ይህ ጭንቀት የአንተ ነው፣ የኔ አይደለም፤ አንተ ስለምትሸከምልኝ ላንተ ሰጥሃለሁ" ልትሉ ይገባል። በዚህም፣ የጌታን ንጥረ-ነገር ወደ ውስጣችሁ ትቀበላላችሁ፤ ገንቢ-አፍራሽ ቅንባሮም በውስጣችሁ ያለማቋረጥ ይሠራል። ከዚህም የተነሣ፣ በውጫዊ መንገድ በእናንተ በኩል የሚገለጠው ክርስቶስ ይሆናል። ክርስቶስን መኖር ይህ ነው። **ይህንን ምሥጢር የማያውቁ ክርስቶስን መኖር ከባድ ነገር እንደሆነ ያስባሉ። በእርግጥ የሚያስፈልጋችሁ ያለማቋረጥ ከጌታ ጋር መነጋገርን በተግባር መለማማድ ነው፤ ያን ጊዜ፣ ያለ ምንም ጥረት ክርስቶስን ትኖራላችሁ።**"—(The Organic Aspect of God's Salvation, pp. 54-55)